
ADV2

## አዲስ የልማት ራዕይ
## አዲስ ቪዥን ለርኒንግ ማቴሪያልስ ማኑፋክቸሪንግ

Addis Development Vision

# የስሜት ህዋሳት ማዳበሪያ ትምህርት



አዲስ አበባ
ጥር 2003 ዓ.ም መጀመሪያ ታተመ
መስከረም 2009 ዓ.ም እንደገና ታተመ

..ማወቅ የሚገባዎት ትልቅ ቁም ነገር!

Addis Development Vision



አዲስ ዴቨሎፕመንት ቪዥን/ አዲስ ቪዥን ለርኒንግ ማቴሪያልስ ማኑፋክቸሪንግ በሙያ ስልጠና ማዕከሉ ዉስጥ የህፃናት ትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማምረት ለኢንተርናሽናል፤ ለመንግስታዊና ለግል መዋዕለ ሕፃናት ድርጅት የትምህርት መርጃ መሳሪያ ገዢዎችን ጥያቄ በማስተናገድ ላይ ይገኛል፡፡



የወቅቱን የሕፃናትና ልጆች እዉቀት ለማስጨበጥ ያስችላሉ የተባሉትን ማስተማሪያ አዲስ ዘይቤ ያካተተ መሆኑ አስተማማኝ ያደርገዋል፡፡

ምርታችን ጥራት አስተማማኝና ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቀ ሲሆን በትምርትና በሞያ ስልጠና የተሰማሩ ባለሙያዎች የረጅም ጊዜ ልምድ ዉጤት ነዉ፡፡



መርጃ መሣሪያዎቹ የዘመናዊ ትምህርት አሰጣጥ ስልትን ያገናዘቡ በመሆናቸዉ ለመዋዕለ ሕፃናትና ዕድሜያቸዉ እስከ 10 ዓመት ለሆናቸዉ ታዳጊ ልጆች ማስተማሪያነት ማገልገል ያስችላል፡፡

በተጨማሪም ድርጅታችን በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀምና ለመዋዕለ ሕፃናት መምህርነት ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡

ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ በርካታ ት/ቤቶች ተጠቅመዉ በዉጤቱ ሲረኩበት በምርታችን እንኮራበታለን፡፡ እናንተም ተጠቀሙበት ዉጤታማነታችሁን ያሳድጋል፡፡

ISBN 978-99944-861-4-4

Printing by:- Star Printing Press

# መግቢያ

ሕፃናት በተፈጥሯቸው አንድ ነገር ላይ ትኩረት ሰጥተው ረዘም ላለ ጊዜ የመቆየት ትእግሥት አይኖራቸውም፡፡ በአንድ ሥፍራ ተቀምጠው ለሰዓት መቆየት ለሕፃናቱ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ለምሳሌ ለሕፃናት ተረት ወይም ታሪክ እየተነገራቸው እያለ ታሪኩ ወይም ተረቱ ትንሽ ረዘም ያለ ከሆነ ሕፃናቱ ይቁነጠነጣሉ፡፡ እርስ በርስ ማውራት ይጀምራሉ፡፡ ነገር ግን ሕፃናት በንቁነት እንዲንቀሳቀሱ ፈቅደንላቸው የሚሠሩትን ሥራ ብንመለከት በአንድ ነገር ላይ ትኩረት ሰጥተው ከማከናወን ይልቅ የሚያዩትን ነገር ሁሉ መነካካትና መሞከርን ይፈልጋሉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ደግሞ ሕፃናቱን የበለጠ እንዲሳተፉ ፍላጎት እንዲያድርባቸውና የተፈለገውን ግብ እንዲመቱ ከፍተኛ አስተዋጽዎ ያደርጋል፡፡

ሕፃናት እየሰሩ ወይም እየተጫወቱ ሲማሩና በቃል ሲማሩ የሚታየው ውጤት የተራራቀ እንደሆነ ስለ ህፃናት የትምህርት አቀባበል ያጠኑ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሰውን የበለጠ ለመግለፅ **ሕፃን የሰማውን ይረሳል፣ ያየውን ያስታውሳል፣ የተገበረውን ያውቃል ይላሉ**፡፡ ስለዚህ ዘመናዊ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በቃል ከሚሰጥ ትምህርት ይልቅ በተግባር እየሠሩ እንዲማሩ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ሕፃናቱ የተሻለ እውቀት ጨብጠው እንዲወጡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ህፃናት ራሳቸው ያከናወኑትን ክንዋኔ ወይም ግኝት መምህራን ከሚነግሯቸውና በቃል ከሚያስተምሯቸው በተሻለና በበለጠ ያስታውሳሉ፡፡ ለምሳሌ ከድንጋይ ይልቅ መስታወት በእጅ ሲነኩት ይለሰልሳል ብሎ ከመንገር ይልቅ በጥያቄ መልክ የትኛው ይለሰልሳል ሞክሩና ተናገሩ ቢባሉ ራሳቸው ሞክረው መልሱን ስለሚያገኙ አይረሱትም፡፡

የአፀደ ሕፃናት ትምህርት ዓላማ ለሕፃናት ስብዕናና እድገት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት አካላቸው፣ ስሜታቸውንና ማህበራዊ ኑሯቸውን በተመለከተ ተገቢውን ዕውቀት ለመጨበጥ መሠረት መጣል ነው፡፡ ይህ መሠረት የሚጣለው ደግሞ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ክንዋኔዎችን ሥርዓት ባለው መንገድ፣ በቅደም ተከተልና መልክ-በያዘ ሁኔታ ሲያከናወኑ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ በመሆኑም አዲሱ ትውልድ ተመራማሪ፣ አምራችና በራሱ የሚተማመን ብቁ ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ አቅጣጫ በመቀየስ በኩል ይህ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡

የሰው ልጅ በተከፋፈለ የእድገት ዘመን ውስጥ ሲታይ የመጀመሪያው የሕፃንነት ዘመኑ ፈጣን የአእምሮ እድገት የሚታይበት ወቅት ነው፡፡ ሕፃናት እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ የእድገት ፍጥነት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ የሁሉም ሕፃናት የአካል፣ የአእምሮ፣ የማስተዋልና የማገናዘብ ዕድገትና ብቃታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያለ እንደሚሄድ ግልፅ ነው፡፡ ብዙ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት ለአንድ ሕፃን የዕድገት ፍጥነት ከፍተኛነትና ዝቅተኝነት ወሳኝ ከሆኑት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ የረዳቶቻቸው ወይም የመምህራኖቻቸው ብቃት ነው፡፡ ስለዚህ የእነዚህ መምህራን እውቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ ዕውቀት ማዳበሪያ ተሀድሶዎች፣ አጫጭር ስልጠናዎችና ሴሚናሮች ማደግና መጎልበት ተገቢ ነው፡፡

የቅድመ ሕፃናት ትምህርት መርሃግብር ተሳታፊ ሕፃናት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ጥቅሞች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

ሀ. በጥራትና በወቅቱ (በዕድሜአቸው) ትምህርት የማግኘት ዕድል ይኖራቸዋል፡፡

ለ. ከክፍል ወደ ክፍል ሳይዛወሩ ቀርተው የሚደግሙትንና ከት/ቤት አቋርጠው የሚወጡትን ተማሪዎች ቁጥር ይቀንሳል፡፡

ሐ. በትምህርታቸው ብቁና ተወዳዳሪ ይሆናሉ፡፡

መ. ማህበረሰባዊና ውስጣዊ ዕድገትን ያዳበራል

ሠ. በሕፃኑና በቤተሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳድጋል ::

ረ. የሴቶችን የተሳትፎ ደረጃ (በተለይ የእናቶችን) ከፍ ያደርጋል::

የሕፃኑ የአእምሮ እድገት ለወደፊት ሕይወቱ በጣም ወሳኝ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ የአእምሮ ጤንነት፣ የመማርና የማደግ፣ (የባሕሪ ለውጥ) እጅግ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው:: በዚህ ወቅት በጥንቃቄና በብቃት የተያዘ ሕፃን በት/ቤት ውስጥ በውጤቱ አመርቂ፣ ክህሎቱን በተሻለ ሁኔታ የሚያሳድግ፣ እንዲሁም በማህበረሳባዊና በኢኮኖሚ እድገቱ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ የተረጋገጠ ነው::

የአፀደ ሕፃናት ዕድገት መርሃግብር መምህራን ለሕፃናቱ እንደ ወላጅ (እናት) እንደ ተንከባካቢና መሪ በመሆን ያገለግላሉ:: ከላይ የተገለፁትን እጅግ ጠቃሚና ወሳኝ ውጤቶችን ለማግኘት ሕፃናት በራሳቸው ያለማንም ጣልቃ ገብነት (የረዳቶቻቸው እርዳታ ግን አይለያቸውም) በየቀኑ ለሰዓት ፀተመስጦ የሚሰሩት ተግባራዊ ስራ ለሕፃናቱ

- ➢ በነፃነት ያለምንም ፍርሃት አስፈላጊውን ስራ እንዲሰሩ ያደፋፍራል::
- ➢ እራስን መምራት ያስተምራቸዋል::
- ➢ ከሕይወት ጋር ያላምዳቸዋል::
- ➢ ያላቸውን ግዴታ እንዲወጡ ያደርጋቸዋል::
- ➢ የሰውነት  እንቅስቃሴያቸውን ያዳብራል::

ወላጅና የሕፃናቱ መምሕራን ለዚህ ውጤት መምጣት ከፍተኛ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል:: ለምሳሌ ሕፃናት የሚያድጉበትን አካባቢ በጥሩ ሁኔታ ማመቻቸትና ሕፃናቱ የሚሠሩትን ሥራ ማዘጋጀት፣ በሚሠሩበት ወቅት በቅርብ ዕርዳታ መስጠትና ማበረታታት የመሣሠሉት ተግባራትን ያከናውናሉ:: አዋቂዎች የልጆቻቸውን ማንነት ለመፍጠር ያላቸው ሚና ቀላል ባይሆንም ሙሉ በሙሉ የወላጆች አስተዋፅኦ ለማለት ያስቸግራል:: ማንነታቸውን ሊገነቡ የቻሉት  ልጆቹ በራሳቸው ሙከራና ጥረት ሲሆን ውጤቱ ያማረ ይሆናል:: ሕፃናት ዕውቀትን በራሳቸው ወደ ራሳቸው ያመጣሉ:: ይህን ያመጡትን እውቀት ከአእምሯቸው ሳይጠፉ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ አብሯቸው ይኖራል:: የስነ ልቦና አዋቂዎች እንደሚሉት አንድ ሕፃን ዕውቀትን መጣጭ አእምሮ የሚኖረው ከተወለደ እስከ 6 ዓመት ነው:: ስለዚህ እነዚህን ሕፃናት መንከባከብና በብቃት ማዘጋጀት ይኖርብናል:: ለሕፃናት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሕፃናት በራሳቸው ሠርተው እንዲማሩ የሚረዳ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን መከተል እጅግ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ በጥናት ተረጋግጧል::

በዚህ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ የህፃናትን ፍላጎት ለማሟላት ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ከልደት እስከ 2½ ዓመት፣ ከ2½ ዓመት እስከ 6½ አመትና ከ6½ አመት እስከ 12 ዓመት በሦስት ደረጃዎች በመከፋፈል ይመለከታል:: ሕፃናት የሚማሩት በእንቅስቃሴ (በመመራመር) በመስራት፣ ቅደም ተከተል በመጠበቅ፣ በመደጋገም፣ በምናብና በረቂቅ በግንኙነት እንደሆነ ያስረዳል:: ህፃናት የመጀመሪያዎቹን ሁለቱ የዕድሜ ደረጃዎችን የስሜት ሕዋሳቶቻቸውን ማለት መንካት ማየት፣ መስማት፣ ማሽተትና መቅመስን በመጠቀምና ቁሳቁሶችን በመፍታትና በመገጠም መፍትሄ በመሻት ሲማሩ ከ6 ዓመት እስከ 12 ዓመት ያሉት ግን ረቂቅ የሆኑትን አዲስ በዳበረው ምክንያታዊነት፣ ግምታዊነት እንቅስቃሴ በመምርከዝ ዕውቀታቸውን ያዳብራሉ:: እነዚህን ሕፃናት ለመርዳት ተስማሚና አመቺ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ያስፈልጋሉ:: መምህራን ዘዴውንና አጠቃቀሙን ካሳዩ በኋላ ሕፃናቱ ራሳቸው በነፃነት

የትምህርቱን ርዕስ እንዲመርጡ ይበረታታሉ። የትምህርት መርጃ መሳሪያዎቹ ከዚህ እንደሚከተሉት አምስት ዋና ክፍሎች ይኖሩታል።

I. የተግባራዊ እንቅስቃሴ መርጃ ሠሳሪያዎች

II. የስሜት እንቅስቃሴ መርጃ መሳሪያዎች

III. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

IV. የሒሳብ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

V. የሳይንስ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

# <u>የስሜት ህዋሳት ትምህርት መርጃ መሳርያዎች</u>


እነዚህ ቁሶች የአንድን ሕፃን ተፈጥሮአዊ ስሜት ቅርጽ በማስያዝ ለማሳደግ በጥንቃቄ የተዘጋጁ ናቸው:: የተዘጋጁትም የሕፃኑን የአእምሮ እድገት ለማፍጠን ሲሆን የማሰብ ችሎታውን ለማዳበርና የስሜት ሕዋሳቶቻቸውን እድገት ለማገዝ ነው::

እነዚህ የስሜት ሕዋሳት ዕድገት አጋዥ ቁሶች የተዘጋጁት የሕፃን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ሕፃናቱ ምላሽ እንዲያገኙ ለማስቻል በሚያመች መልኩ የተዘጋጁ ናቸው:: ለምሳሌ የቀጭንና ወፍራምን፣ አጭርና ረጅምን፣ ጠፋጭና መራርን፣ ሸካራና ለስላሳን፣ ጥሩ ሽታና መጥፎ ሽታን የመሳሰሉትን ለይተው እንዲያውቁ የሚረዳ የትምህርት ክፍል ነው:: አንዴ እነዚህን በስሜት ሕዋሳቶቻቸው ለይተው ማወቅ ከጀመሩ ደስተኛችና ሙሉነት እየተሰማቸው ይሄዳል:: የስሜት ሕዋሳቶቻችንን ተጠቅመው አካባቢያቸውን የሚረዱባቸው ዋነኛ መገናኛ ድልድይ ናቸውና ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን:-

## 1. <u>እጀታ ያለው ሲሊንደር</u>



<u>መርጃ መሳሪያ</u>:- አራት የእንጨት ቅርጾች ሁሉም እኩል መጠን ያላቸው ማለት እርዝመታቸው 55 ሴ.ሜ፣ ቁመታቸው 5 ሴ.ሜ እና ወርድ ደግሞ 5 ሴ.ሜ መሆን ይኖርበታል:: እያንዳንዱ ቅርጽ ሁለት ሲሊደሮች ሲኖሩት፣ እነዚህም ከቀዳዳው መጠን ጋር እኩል መሆን ይኖርባቸዋል:: ሲሊደሮቹ ለመያዝ የሚያመች መያዣያ ይኖራቸዋል::




<u>ስብስብ 1</u>: ሁሉም ሲሊደሮች ቁመታቸው 5 ሴንቲ ሜትር ሲሆን ነገር ግን ዲያሜትራቸው አንዱ ከሌላው በግማሽ ሴንቲ ሜትር የቀነሰ ከ5 ሴንቲ ሜትር እስከ ግማሽ ሴንቲ ሜትር ድረስ ይረዝማል::

<u>ስብስብ 2</u>: - በዚህ ስብስብ አንዱ ሲሊንደር ቁመትና አንዱ ዲያሜትር ከሌለው ቁመትና ዲያሜትር መለየት አለበት ከ5 ሴ.ሜ ቁመትና 5 ሴ.ሜ ዲያሜትር ወደ ግማሽ ሴ.ሜትር ቁመትና በግማሽ ሴ.ሜትር ዲያሜትር መለያየት አለባቸው::



<u>ስብስብ</u> 3:-በዚህ ስብስብ ውስጥ ያሉት ሲሊንደሮች ዲያሜትራቸው ከ5 ሴ.ሜ ወደ 1/2 ሴ.ሜ ሲቀንስ ቁመታቸው ግን ከ1/2 ሴ.ሜ ወደ 5 ሴ.ሜ መጨመር ይኖርበታል::



<u>ስብስብ</u> 4:- ቀጥሎ ያሉት ሲሊንደሮች ቁመታቸው ከ5 ሴ.ሜ ወደ 1/2 ሴ.ሜ ሲቀንስ ዲያሜትራቸው ግን $2^{1/2}$ ሴ.ሜ. መሆን አለበት::

አቀራረብ፡

- የሚሰራው ጠረጴዛ ላይ ነው
- ሕፃናት አብረዋችሁ እንዲሠሩ አበረታቷቸው
- (ቅርጽ) አንድን በመምረጥ ሕፃናቱ አንዱን በአንድ እጃቸው ሌላውን በሌላ እጃቸው እንዴት እንደሚይዙ ማሳየት
- የእቃውን ስም ለልጆቹ መንገር
- ሲሊንደሩን ከቅርጽ አንድ በየተራ ማስወገድ
- አውራጣት፣ የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን በመጠቀም ከመጨረሻው በመነሳት ጠረጴዛው ላይ ማስቀመጥ
- በየጊዜው ቀዳዳውን በመመልከት ከሲሊንደሩ ጋር ማወዳደር
- ሲሊንደሩን በተገቢው ቦታ መመለስ
- ከመጨረሻው በመጀመር ሲሊንደሩ ቀዳዳው ውስጥ እስኪ.ተካ መቀጠል

መልመጃ 1

1. ሕፃኑ እንዳየው እንዲሞክር ማድረግ
2. ተግባሩን በሁለተኛ ቅርጽ (Block) ማስቀጠል
3. ተመሳሳይ ሙከራን በሶስተኛው ቅርጽ ማስቀጠል
4. ሙከራውን በ4ኛው ቅርጽ (Block) ማስቀጠል
5. ሕፃኑ ሙከራዎችን ተራ በተራ ካከናወነ በኋላ ሲሊንደሩን ቦታው መመለስ
6. እያንዳንዱን ሲሊንደር በመውሰድ፣ ሲሊንደሮቹ እንዴት እንደሚደባለቁ ለሕፃናቱ ማሳየት
7. በቀዳዳዎቹ ውስጥ ማስገባት
8. ሁለቱን ቅርጾች (Blocks) ከአራተኛው በስተቀር በመውሰድ ጠረጴዛው ላይ በሶስት ጎን ቅርጽ ማስቀመጥ
9. ሁሉንም ሲሊንደሮች አስወግዶ በጠረጴዛው መካከል ማስቀመጥ
10. በተገቢው ቀዳዳ መተካት (ቦታው መመለስ)

መልመጃ 2

- ሦስት ቅርፆችን (Blocks) መውሰድ
- ጎነ ሶስት ቅርፅ ሲኖረው መሠረቱ ወደ መምህሩ መሆን አለበት
- ሁሉንም ሲሊንደሮች ማስወገድ
- ጎነ ሶስት ምስል መካከል ማስቀመጥ
- በተገቢው ቀዳዳ ውስጥ መተካት

መልመጃ 3

- አራቱን ቅርፆች (Blocks) መውሰድ
- ምንጣፍ ላይ ወይም ወለሉ ላይ በካሬ ቅርጽ ማስቀመጥ
- ሁሉንም ሲሊንደሮች አስወግዶ በካሬው መካከል ማስቀመጥ
- በተገቢው ቀዳዳቸው ውስጥ መተካት

ቀጥተኛ ዓላማ፡

- መጠናቸውን ይለያሉ

ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ፡

- ምክንያታዊነትን በማዳበር ስህተቶችን ማረም ይችላሉ
- በነፃነት የራሳቸውን ተግባራት ይገመግማሉ

**የቋንቋ ዕድገት:-**

- በእጅ የመያዝ ዕድገትና ጣቶቹ ለመፃፍ ዝግጁ መሆን
- ለሕፃናቱ የምንጠቀምበትን ነገሮች መንገር የቃላት ችሎታቸውን ያዳብራል

**ለሂሳብ መዘጋጀት:-**

- እቃዎቹን በቅድም ተከተል ማዘጋጀት አንድ ለአንድ ያለውን ግንኙነት መለማመድ


**ዕድሜ:-**

እንደ ልጆቹ ሁኔታ ከ3 ዓመት ጀምሮ ይሆናል

## ፪. ሮዝ ፎቅ (PinkTawer )

**መርጃ መሳሪያ**

- 10 ሮዝ የእንጨት ኪዩቦች የተለያዩ ሦስት ዲያሜንሽን ያላቸው ሲሆን እያንዳንዱ ኪዩብ በአንድ ኪዩቢክ ሴ.ሜ ይበላለጣል
- ትንሹ 1 ኪዩቢክ ሴ.ሜ ሲሆን ትልቁ 10 ኪዩቢክ ሴ.ሜ ነው::



**አቀራረብ**

- የዕቃውን ስም ማስተዋወቅ
- ምንጣፍ ሕፃናቱ እንዲያነጥፉ መንገር
- ኪዩቡን እንዴት እንደሚይዙት መጀመሪያ ማሳየት ከዚያም ከምንጣፉ በቀኝ በኩል እንዲያስቀምጡ መንገር
- የልጆቹን እርዳታ መጠየቅ
- ትልቁን ኪዩብ ከስር በሁለት እጅ ደግፎ መያዝ
- ከሕፃናቱ ጋር በመቀመጥ ትልቁን ኪዩብ መምረጥ
- ከሌሎቹ ኪዮቦች ጋር ማወዳደር
- ምንጣፉ ላይ ለይቶ ማስቀመጥ
- ቀጥሎ ያለውን ትንሹን ኪዩብ መምረጥና ከሌሎች አንድና ሁለት ኪዮቦች ጋር ማወዳደር
- አስተካክሎ ወዲያው ማስቀመጥ
- ትልቁ ኪዩብ መሐል ላይ መሆን ይኖርበታል
- የሚቀጥለውን የመጨረሻ ኪዩብ በመምረጥ ግንባታውን መቀጠል
- ትክክለኛውን ኪዩብ በመምረጥ ግንባታውን መቀጠልና አንዳንድ ጊዜ ማወዳደር
- ያሉትን በሁሉም አንግሎች መመልከት
- ተራ በተራ ኪዩቦቹን መለያየት
- ከትልቁ ኪዩብ በመጀመር እንዴት አድርገው ወደ ነበረበት ቦታ እንደሚመልሱ ማሳየት

**መልመጃ 1**

- ጠለሉ ምንጣፍ ላይ በተቀመጠው ኪዩብ መጀመር
- ማማ መስራትና ከዚያ አንዱ ኮርነር ከሌለኛ ሁለት ጎኖች መግጠማቸውን መመልከት
- የተገጣጠሙትን ጎኖች ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ በትኩረት መረዳት
- ማማውን ስትሰሩ ሕፃናቱ የተገጣጠሙት ኰኖችና መስመሮች እንዲመለከቱ አድርጉ
- ማማ ሲሰራ ደረጃዎቹ መታየት አለባቸው
- እያንዳንዱ ኪዩብ በትክክል መቀመጡን ማረጋገጥ
- ማማው ሲሰራ ትንሹን ኪዩብ ከታች በመጀመር ቀስ በቀስ ሁሉንም ጠርዝ በማስነካት መውሰድ
- ሕፃናቱ እናንተ የምትሰሩትን እንደሚከታተሉ አረጋግጡ

**ቀጥተኛ አላማ**

- በመጠን መለያየታቸውን በመመልከት ይረዳሉ

**ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ**

- ቀጥተኛ የሰውነት አቋምና ትምህርታዊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ
- ሕፃናቱን ለሒሳብ ትምህርት ያዘጋጃል

**የትኩረት ነጥብ**

- የተደረገው እንቅስቃሴ

**ስሕተትን መቆጣጠር:-**

- የሕፃኑ የማየት ብቃቱ እድገት

**ቋንቋ**

- ትምህርቱ የሚሰጠው ልጁ ሮዝ ፎቁን ከሠራ በኋላ ነው
- ትምህርቱ የሚሠጠው በሦስት የማስተማሪያ ዘዴ ነው።
- ትልቅና ትንሽ የመሳሰሉትን ማሳየት

**ዕድሜ**

- ከ3 - 4½ ዓመት

**ጨዋታ 1**

- ሁለት ምንጣፎችን በርቀት ማስቀመጥና አንዱ የያዘውን በሌላ ምንጣፍ ላይ በመሆን እንዳይታይ ማድረግ
- ሕፃናቱ ኪዩቡን ወደ ምንጣፉ እንዲያመጡ ማድረግ
- ትልቁን ኪዩብ መምረጥ
- ወደ ሌላኛው ምንጣፍ መውሰድና ሌላውን በመለወጥ ማምጣት
- ከዚያ ሮዝ ፎቅ መስራት
- ማማው እስኪሰራ ድረስ ሕፃናቱን ተራ በተራ ማሰራት

**ጨዋታ 2**


- ልክ እንደ መጀመሪያው ጨዋታ ምንጣፉንና ኪዩቡን ማስቀመጥ
- አንዱን ኪዩብ መምረጥ
- ኪዩቡንና ሁሉንም ልጆች ወደ ሌላኛው ምንጣፍ መውሰድ
- አንዱን ሕፃን በመምረጥ ትንሹን ወይንም ትልቁን ኪዩብ እንዲያመጣ ማድረግ

- ልጁ ሲመለስ የተጠየቀውን ማድረጉን ማረጋገጥ
- አንዱን ወይም ሁለቱን ኪዩቦች መመለስ
- የሚቀጥለው ልጅ ኪዩቡን እንዲያመጣ ማድረግ
- እስከሚያስፈልግበት ጊዜ ድረስ ድርጊቱን መቀጠል
- ጨዋታውን በተመሳሳይ ሁኔታ መቀጠል፣ ነገር ግን የሚቀጥለውን ትልቁን ወይም የሚቀጥለውን ትንሹን ኪዩብ መጠየቅ

**ማስታወሻ**

- ጨዋታው የሚካሄደው በሦስት ወይም በአራት ልጆች ነው
- ልጆች በትክክል የማያከናውኑ ከሆነ እነርሱ ራሳቸው ጨዋታውን እንዲጫወቱ መተው

## 3. ቀይ ዘንግ (RED RODS)



**መርጃ መሳሪያ:**

- በስፋት እኩል የሆኑ ርዝመት ያላቸው ግን የሚበላለጡ አስር ቀይ ዘንጎች
- በእያንዳንዱ ዘንግ መካከል ያለው የርዝመት ልዩነት 10 ሲ.ሜትር ነው::
- እረጅሙ ዘንግ ርዝመቱ 100 ሴ.ሜትር ነው::

**አቀራረብ**

- ሕፃናቱ ቁሱ ያለበት ቦታ እንዲመጡ መጋበዝ
- የቁሱን ስም መንገር
- ምንጣፋቸውን እንዲያነጥፉ ማድረግ
- የዘንጉን ጎን በሁለት እጆቻቸው በቁመቶቻቸው ቀጥ አድርገው መያዝ
- እያንዳንዱን ዘንግ ሳይመርጡ ትይዩ በማድረግ በምንጣፉ ላይ እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- እረጅሙን ዘንግ ለይቶ ምንጣፉ እናት ላይ ማስቀመጥ
- አንዱን በመምረጥ ከዚያ የሚቀጥለውን ተራ በተራ መያዝ
- በየጊዜው አንዱን ዘንግ ከሌላኛው አንድ ወይም ሁለት ዘንጎች ጋር ማወዳደር
- በመጨረሻው ዘንግ ትይዩ ሌላውን ማስቀመጥና (Slides) ዘንበል በማድረግ ወደ መጨረሻው ዘንግ ትይዩ ማስቀመጥ
- በግራ በኩል ያሉት ተስተካክለው መደርደራቸውን በግራ እጅ ጣቶቻችሁ በመንካት ማረጋገጥ
- ቀጥለው የሚቀመጡትም ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ እነዚህኑ የግራ እጅ ጣት መጠቀም
- ዘንጎቹ ከተቀመጡ በኋላ በተሠራው ሥራ መደሰታችሁን ለልጆቹ አሳዩዋቸው
- በምንጣፉ ዙሪያ ከልጆቹ ጋር በመሆን ዘንጎቹን በሁሉም አንግል መመልከት
- ዘንጉን ከተበተኑ በኋላ ከትንሹ ዘንግ በመጀመር ተራ በተራ ምንጣፉ ላይ እንደገና መደርደር

➲ ሕፃናቱ ተግባራቱን እንዲተገብሩ መጋበዝ

<u>መልመጃ አንድ፡-</u>

➲ በፊት ሲደረግ እንደነበረው ሕፃናቱ ዘንጉን እንዲገነቡ ማገዝ

<u>መልመጃ ሁለት፡-</u>

➲ ከብዙ ጊዜ ልምምድ በኋላ ሕፃናቱ ደረጃዎችን ራሳቸው ይሠራሉ።

➲ ሕፃናቱ የእያንዳንዱን ቀያይ ዘንግ እርዝመት እንዲለዩ ከትልቁ በመጀመር በቅደም ተከተል መደርደር

➲ አጭሩን ዘንግ ከሌላኛው ዘንግ ተቃራኒ በማስቀመጥ መመለስ

<u>ቀጥተኛ ዓላማ፡-</u>

➲ በማየት የርዝመት ልዩነት እንዳላቸው መገንዘብ

<u>ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ፡-</u>

➲ ለሒሳብ ትምህርት ማዘጋጀት

➲ የእጅ ጡንቻ ጥንካሬን ያዳብራሉ

➲ የርዝመት ልዩነቶችን እንዲረዱ ማድረግ

<u>የቁምነገር ነጥቦች፡-</u>

➲ ዘንጎቹን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

➲ አንዱን ዘንግ ከሌላኛው ጋር ማወዳደር

<u>ስሕተትን መቆጣጠር፡-</u>

➲ ልጁ የማየት ብቃቱን ያዳብራል

<u>ቋንቋ፡-</u>

➲ ከተለመደው ውጭ በማየት ብቃት ላይ የተመሠረተ የሦስት ክፍለ ጊዜ መልመጃ መስጠት

➲ አጭር፣ ረጅም የመሳሰሉትን ቃላት ማስተዋወቅ

➲ ከዚያ በመቀጠል

አጭር - በጣም አጭር

ረጅም - በጣም ረጅም

የመሳሰሉት የማወዳደርያ ቃላቶችን ማስተማር

<u>ዕድሜ</u> 3½ - 4½ዓመት

ጨዋታ አንድ

➲ አራት ሕፃናትን ከሕንፃቱ ጋር እንዲሆኑ ጋብዙአቸው

➲ አራርቀው ሁለት ምንጣፎችን እንዲያነጥፉ ንገሩዋቸው

➲ በአንድ ምንጣፍ ላይ ዘንጎች ሳይመረጡ ይቀመጣሉ

➲ ረጅሙን መምረጥ

➲ በሁለቱም እጅ በመያዝ ከሕፃናቱ ጋር ወደ ሚቀጥለው ምንጣፍ መሄድ

➲ ከሌላኛው ምንጣፍ ቀጥሎ ያለውን አጭር ዘንግ እንዲያመጣ መንገር

➲ በየደረጃ መቀጠል-ሕፃናቱ ዘንጉን እንዲያመጡ ማድረግ


<u>መልመጃ 2፡-</u>

➲ ሁለት ምንጣፎችን ልክ እንደ መልመጃ አንድ ማስቀመጥ

- ከሕፃናቱ ጋር በመሆን ዘንጎቹን መርጦ ወደ ሌላኛው ምንጣፍ መውሰድ
- ሕፃኑ ካመጣው ዘንግ የሚበልጠውን እንዲያመጣ መንገር - ይህም መጀመርያ ያመጣውን መልስ ሳይወስድ መሆን አለበት
- ዘንጎቹን በታቸው መመለስ ወይም መተው
- ልጆቹን አጭሩን ዘንግ እንዲመርጡ ማድረግ
- በዚሁ ዓይነት ሕፃናቱ አጭሩን ወይንም እረጅሙን ዘንግ እንዲመርጡ በተከታታይ ማድረግ

## 4. <u>የቀለም ሳጥን -1 (Color Tablets: Box 1)</u>

<u>መርጃ መሳሪያ</u>:



- የመጀመሪያው ሳጥን ስድስት ትናንሽ ባለ ቀለም ሬክታንግል ቅርፆች
- ሦስት የሚገጣጠሙ ዋነኛ ቀለሞች እነርሱም ቀይ፣ ሰማያዊና ቢጫ ናቸው

አቀራረብ

- ምንጣፍ ወይም ጠረጴዛ መጠቀም
- ሕፃኑ ከመደርደርያው ላይ የቀለሙን ሳጥን እንዲያመጣ መንገር
- ምንጣፍ ወይም ጠረጴዛ ላይ እንዲያስቀምጥ ማድረግ
- ሕፃኑ መክደኛውን እንዴት እንደሚከፍትና ሳጥኑን መክደኛው ላይ እንዴት እንደሚያስቀምጥ ማሳየት
- ምንጣፉ መካከል እንደተመቸ ማስቀመጥ
- ሕፃናቱ ወደ መጨረሻው በመምጣት እንዲረዱዋችሁ መጋበዝ
- ቀዩን ወይንም ሰማያዊውን ባለቀለም ሬክታንግል በመምረጥ ምንጣፉ ግራ ጠርዝ ላይ ማስቀመጥ
- የምንጣፉን ወይም የጠረጴዛውን መካከል መመልከት ከዚያም ጓደኛውን (የቀረውን) መፈለግ
- የቀረውን ባለ ቀይ ቀለም ሬክታንግሎችን ከበፊቶቹ ቀኝ ማስቀመጥ
- ልክ የሮማውያን ቁጥር ሁለት (II) ዓይነት መደርደር
- የሚቀጥሉትን ሁለቱን ቢጫ ባለቀለም ሬክታንግሎችን መምረጥ
- እነዚህን ከሰማያዊው በታች ማስቀመጥ
- ቀዩን በዚሁ ዓይነት መቀጠል
- ድርድሩን ከልጆቹ ጋር መመልከት
- ቀለሞቹን መደባለቅ
- ልጆቹ ቀለሙን በጥንድ እንዲያስቀምጡ መንገር፣ በትክክል ሳጥኑ ውስጥ እንዴት እንደሚያስቀምጡ ማሳየት

<u>መልመጃ አንድ</u>:

- ልጆቹ በራሳቸው የአቀራረብን ስራ በመድገም መስራት

<u>ቀጥተኛ ዓላማ</u>:

- ቀለም የመለየት ችሎታን ያዳብራሉ

- ቀድሞ ያላቸውን የቀለም ሀሳቦች ይበልጥ እንዲለዩ መርዳት
- የመረዳት ችሎታን ማዳበር
- ስለሚያዩዋቸው ቀለሞች ቁልፍ ሀሳብ መስጠት

**ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ:**

- ስዕሎችን ቅርፃ ቅርፆችን የማድነቅ ችሎታቸውን ማዳበር
- የመመልከት ችሎታን ማዳበር

**አስፈላጊ ነጥብ:-** ቀለሞችን ማጣመድ

**ስሕተቶችን መቆጣጠር:-**

- በቀለማት መካከል የሚገኘውን ልዩነት
- የመመልከትን
- ቀለሞችን የመለየት ችሎታን ማጤን

**ቋንቋ:-**

- የቀለሞቹን ስሞች በሦስት ክፍለ ጊዜ መስጠት:- ይህም ልጆቹ ጥንዶቹን ከለዩ በኋላ ይሆናል

**ዕድሜ:-**

- 3 ዓመት

**ጨዋታ አንድ:-**

- ልጆቹን በቡድን በመከፋፈል
- ሁለት ምንጣፎች በተለያዩ የክፍሉ መጨረሻ መዘርጋትና አንድ አይነት ቀለም ያላቸውን ጥንድ ባለቀለም ሬክታንግሎችን በእያንዳንዱ ምንጣፍ ላይ ማስቀመጥ
- አረዳት መምህሩ አንዱን ባለቀለም ሬክታንግል ካሳየ በኋላ ሕፃኑ ሌላውን ተመሳሳይ ቀለም ያለውን ከሁለተኛው ምንጣፍ እንዲያመጣ ማድረግ፡፡ ከመጣ በኋላ አንድ አይነቶችን በጥንድ አንድ ላይ በአንዱ ምንጣፍ ላይ እንዲያስቀምጥ ማድረግ

**ጨዋታ ሁለት:-**

- እያንዳንዱን ሕፃን በቡድን ለመከፋፈል ምንጣፍ እንዲያመጡ መንገር
- ለሕፃናቱ የተለያዩ ቀለሞችን እያንዳንዳቸው እንዲያዩት መስጠት
- ሬክታንግሎቹን ምንጣፍ ላይ እንዲያስቀምጡ መንገር
- ሕፃናቱ አንድ ዓይነት ቀለም ያላቸውን ነገሮች ወደ ምንጣፉ በማምጣት እንዲያወዳድሩ ማድረግ
- በተመሳሳይ
  - ሬክታንግላዊ ቀለሞችን በመውሰድ በአካባቢው ካሉት ነገሮች ጋር በማስተያየት ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን መለየት ይህንን ለሁሉም ማድረግና ልጆቹ ሰብስበው ምንጣፉ ላይ ወይም ጠረጴዛው ላይ እንዲያስቀምጡ ማድረግ

## 5. ባለቀም ሁለተኛ ሳጥን (Color Tablets: Box Two)



**መርጃ መሳሪያ:-**

- 22 ባለቀለም ሬክታንግሎችን በተከደነ ሳጥን ውስጥ
- ዋነኛ ቀለሞች - ሰማያዊ፣ ቢጫና ቀይ

- ሁለተኛ ቀለም - አረንጓዴ፣ ብርቱካናማና ወይንጠጅ
- ሦስተኛ ቀለም - ብራውን ሀምራዊና ግራጫ
- ጥቁርና ነጭ ቀለሞች የተለያዩ ናቸው።

**ማስታወሻ:-**

አቀራረቡ፣ መልመጃውና ጨዋታው ከመጀመሪያው ከቀለም ሳጥን ጋር ተመሳሳይ ነው።

**ቀጥተኛ ዓላማ:-**

- ቀለም የመለየት ችሎታን ማዳበር
- ሕፃኑ ስለ ቀለም ያለውን እውቀት በአይነት መከፋፈል

**ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ**

- በስዕልና በንድፍ ላይ ያለውን አድናቆት ማዳበር
- የምልከታ ችሎታቸውን ማዳበር
- በአካባቢው ያለውን ቀለሞች ማድነቅ

**የትኩረት ነጥብ:-**

- ቀለሞችን ማጣመድ

**ስሕተት አቆጣጠር**

- በቁሶቹ ውስጥ
- በመመልከት መረዳት
- የቀለሞችን ልዩነት መለየት መቻል


**ቋንቋ:-**


- የሁለተኛውን ሳጥን ቀለሞች በሦስት ክፍለ ጊዜ ማስተማር

**ዕድሜ:-**

- ሕፃኑ በሳጥን አንድ በቂ ልምድ ካዳበረ በኋላ

## ፮. የጂኦሜትሪ ሳጥን (Geometric Cabinet)







**መርጃ መሳሪያ:-**

- ማቅረቢያው ትሪ የተሰራው በእንጨት ሲሆን አራት ካሬ ክፍሎች፣ ሦስት ካሬዎችና ትሪያንግሎችን የያዘ ነው
- በውስጥ በኩል መሃሉ ላይ ትሪውን ለማንሻ መያዣ ይኖረዋል።
- ሳጥኑ (Cabinet) ስድስት መሳቢያዎች ሲኖሩት እያንዳንዳቸው የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ይዘዋል።
  1. ሶስት ጎን፣ ሞላላ፣ ኤሊፕስ እና የወረቀት ወይም የቆርቆሮ ሺት ቅርጽ
  2. ሮምበስ፣ ትራፒዝየም፣ ፓራሌሎግራምና ቋሚ አንግል ትራፕዝየም
  3. ስድስት ክቦች ዲያሜትራቸው ከ10 ሳ.ሜ እስከ 5 ሳ.ሜ የያዘ መሳቢያ


4. ሌላኛው መሳቢያ ስድስት ባለ አራት ጎን ካሬዎች፡- ከአምስት ሬክታንግሎች ርዝመታቸው ከካሬው ጋር እኩል ሲሆን ጎናቸው ግን ከ10 ሳ.ሜ ወደ 5 ሳ.ሜ ዝቅ እያለ ይሄዳል




5. የሚቀጥለው መሳቢያ ደግሞ የተለያዩ ስድስት ሶስት ጎናም ምስል፣ ሁሉም በጎናቸው ርዝመት ወይም በአንግሎቻቸው ስፋት የተለያዩ ናቸው:: እነርሱም ሶስቱም ጎኖች እኩል የሆነ ሶስት ጎን (ኢኪዊላተራል ትሪያንግል)፡- ሁለቱ ጎኖቹ እኩል የሆኑ አንዱ አንግል 90 ድግሪ (አይሶስለስ ራይት አንግል ትሪያንግል) የሆነ ምስል፣ ሁለት ጎኖቹ እኩል የሆኑና አንዱ አንግል ከ90 ዲግሪ በታች የሆነ ሶስቱም ጎን ምስል፣ ሁለት ጎኑ እኩል እያንዳንዱ አንግል ከ90 ዲግሪ በላይ ከ180 ዲግሪ በታች የሆነ ሶስት ጎን ምስል፣ ሶስቱም የተለያየ ርዝመት ያላቸው ባለ 90 ዲግሪ አንግል ሶስት ጎናምና (እስካለን ትሪያንግል) ሶስቱም ጎኖች የተለያየ ርዝመት ያላቸው አንግላቸው ከ90 ዲግሪ በታች የሆነ ሶስት ጎናም ምስሎች ናቸው::




1. ሁሉም ጎናቸውና አንግላቸው እኩል የሆኑ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝና አስር ጎናም ምስሎችን የያዘ መሳቢያ






- ሦስት ስብስብ ካርዶች በእያንዳንዱ መሳቢያ
    1. ሁሉም ስዕሎች በካርዱ ላይ በሰማያዊ የታተሙ ናቸው
    2. ስዕሉ የተሠራበት መስመር ሰማያዊ መስመር በ1/2 ሴ.ሜ ውፍረት
    3. ስዕሉ በግልጽ ሰማያዊ ቀለም የተሰራ
- ካርዶች በሦስት ትናንሽ ሳጥኖች ውስጥ ይከፋፈላሉ
- ሳጥኑ ሙሉ በሙሉ በሁለተኛ ወፍራም መስመርና በሦስተኛ ቀጭን መስመር በተሰሩ ካርዶች የተሞላ ነው::



**አስፈላጊ ነጥቦች:-**

- የተለያዩ ስዕሎችን መንካት
- ተገቢ ካርዶችን ማሰባሰብ
- በተጨባጭ ያሉትን ከስዕሉ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ዕቃዎች ማሰባሰብ
- በአካባቢው ተስማሚ ቅርፆችን መፈለግ



**<u>ስሕተትን መቆጣጠር</u>: -**

- ቁሱ በቀጥታ ተስማሚ መሆኑ
- በመቀጠል የሕፃኑ የማየት ችሎታ መዳበርና መለየት መቻል

**<u>ዕድሜ</u>:-**

- 4 ዓመትና ከዛ በላይ

አቀራረብ ሀ

- ሕፃኑን በመጥራት ቀስ የት እንዳለ ማሳየት
- እንዴት መያዝ እንዳለበት ለሕፃኑ ማሳየት
- የሳጥኑን መሰቢያ ወይም የማቅረቢያን ትሪ ጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
- አንዱን ቅርጽ ከትሪው ላይ በቀኝ እጅ መያዣያውን በመያዝ የቀሰሙን ጎን ማሳየት
- ጠረጴዛው ላይ ማስቀመጥ
- በቀኝ እጃችን መቆንጠጫ ጣቶቻችን ሁሉንም የገቡትን ተጨማሪ ነገሮች ጠርዞቻቸውን አንድ ዙር መንካት
- የትሪውን ዙሪያ ውስጠኛ ክፍል በመንካት ከውስጥ ያሉትን ተጨማሪ ነገሮች አሁንም እንደገና መርዳት
- ሁልጊዜ በአንድ ተከታታይ እንቅስቃሴ መርዳት
- ሕፃኑን ለእርዳታ መጋበዝ
- ተጨማሪውን ነገር በፍሬሙ ውስጥ መተካት
- ሕፃኑ እንቅስቃሴውን ከጨረሰ በኋላ እንዴት ቦታው ላይ እንደሚመልስ ማሳየት

አቀራረብ ለ

- ማቅረቢያውን ትሪ በመጠቀም ሁሉንም ቅርፆች ሕፃኑ እንዲደበላልቃቸው መርዳት
- አንዱን ቅርጽ በመውሰድ በቀኝ እጅ በመቆንጠጫ ጣቶቻችሁ መዳሰስ
- ፍሬሙን በመዳሰስ ቅርፁን ቦታዉ (ፍሬሙ) ውስጥ መመለስ
- በተቀሩት ቅርፃ ቅርፆች ተመሳሳይ ተግባሮችን ማከናወን
- ከዚያ ሕፃኑ እንደ እናንተው እንዲያከናውን መጋበዝ
- ሕፃኑ ቁሱን ቦታው እንዲመልስ መንገር

**መልመጃ 1: -**

- ሕፃኑ ከላይ የተመለከተውን ዓይነት አቀራረብ ያሳያል

**መልመጃ 2: -**

- ሕፃኑ በግሉ በሁሉም ማቅረቢያ ይሰራል

**መልመጃ 3: -**

- ሕፃኑ ሁለት ማቅረቢያ ላይ ያሉትን በመቀላቀል ይሠራል
- ሕፃኑ ማቅረቢያውን በመጨመር ክንዋኔውን ይፈፅማል
- ምንጣፍ ላይ ሁሉንም ማቅረቢያ በአንድ ላይ በማድረግ ይሠራል።

**ቀጥተኛ ዓላማ:-**

- የመመልከት ችሎታን ማዳበር
- የቅርፃ ቅርፆችን ስም መማር
- ለሒሳብ ትምህርት መዘጋጀት

**ኢ. ቀጥተኛ ዓላማ፡-**

- ለጽሕፈት ዝግጁ መሆን

**ቁምነገሩ፡-**

- የነበረው እንቅስቃሴ
- የተለያዩ ቅርፃቅርፆችን መለየት
- ተግባሩ
- ከአካባቢው ጋር መያያዝ

**ቋንቋ፡-**


- የቅርፃ ቅርፆችን ስም በሦስት ክፍለ ጊዜ ማስተማር (ሕፃናት ካርዱን መጠቀም ሳይጀምሩ የቅርጾቹን ስም ማወቅ የለባቸውም)

**ዕድሜ**

- ከ 4½ ዓመት በላይ

## ፯. መሰራች ጎነ ሦስት ሳጥን 1 (Constructive Triangles: box 1)

**መርጃ መሳሪያ፡-**



- አንድ ጥንድ ትልቅ አረንጓዴ ጎነ ሦስት ፤ ካሬ የሚመሰርቱ
- ሁለት ብጫ ሦስት ቅርፆች ሦስት ጎናም ለመሥራት
- ሁለት ግራጫ ጎነ ሦስት ቅርፆች ሦስት ማዕዘን ለመስራት
- ሁለት አረንጓዴ ጎነ ሦስት ቅርፆች ፓራሌሎግራም ለመስራት
- ሁለት ጎነ ሦስት ቅርፆች ሬክታንግል ለመስራት
- ሁለት ጎነ ሦስት ቅርፆች ትራፒዝየም ለመስራት
- የሁሉም ጎነ ሦስት ቅርፆች ዳርና ዳር ላይ ጥቁር መስመር አለው

**አቀራረብ፡-**

- የማስተዋወቁ እርምጃዎች እንዳለፈው አይነት አቀራረብ ይሆናል
- ቁሱን መንገር
- ሦስት ጥንድ ጎነ ሦስት ስንመርጥ የመጀመሪያውን ካሬ ለመስራት አረንጓዴውን ጎነ ሦስት እንመርጣለን
- ሁለተኛ ሁለት ግራጫ ጎነ ሦስት ምስሎች ሬክታንግል ለመስራት ያስፈልጋሉ
- በሦስተኛ ሁለት ብጫ ሦስት ቅርፆችን በመጠቀም ሮምበስ ለመስራት
- ምንጣፍ ላይ መዘርጋት
- ሕፃኑ ሳጥኑን ይቆልፍና ወደ ጎን ያስቀምጥ

- ሁለት አረንጓዴ ጎነ ሦስት በመውሰድ በተቀራኒ ማጋደም፣ ሆኖም ጥቁሩ መስመር ትይዩ ሆነው በእናንተና በሕፃናቱ ፊት መታየት አለባቸው።
- በሁለቱም እጆቻችሁ ጠቋሚና መሀል ጣት በእያንዳንዱ ሦስት ጎኖም ላይ ያሉትን ጥቁሩን መስመር ቀስ እያላችሁ መጠቆም
- ቀስ እያላችሁ ሦስት ማዕዘኑን ማጠጋጋት
- በመሃላቸው ያለው ርቀት እየቀነሰ ሲሄድ፣ ሦስቱን ማዕዘን ቅርፆችን በመገጣጠም ካሬ መስራት
- ካሬውን በተማሪዎቹ ፊት ለፊት ምንጣፉ ላይ ማስቀመጥ
- በተመሳሳይ መንገድ ለመቀጠል የሚቀጥሉት ሁለት ቅርፆችን ማስተዋወቅ
- ሕፃኑ ተመሳሳይ ተግባር እንዲያከናውን መጋበዝ
- ሕፃኑ ከጨረሰ በኋላ የተቀሩትን ሁሉንም ቅርፆች ማስተዋወቅ
- ትራፐዝየሙን በሳጥኑ ውስጥ መተው
- ሁሉንም ቅርፆች መቀላቀል። ሕፃናቱም እንዲያዛምዱ መጋበዝ
- በመጨረሻ ትራፕዝየሙን ማስተዋወቅ
- ለሕፃኑ ቅርፃ ቅርፆቹ በቅደም ተከተል እንዴት ማስቀመጥ እንደሚችል ማሳየት
- በመጀመሪያ ትራፐዝየም፣ ከዚያ ቢጫ ጎነ ሦስት ከአረንጓዴው በላይ ማስቀመጥ።
- በመጨረሻ ሦስት ቅርፆችን ማለት ግራጫ፣ አረንጓዴ እና ቢጫ ጎነ ሦስት በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ናቸው።

**ቀጥተኛ አላማ**

- ሦስት ማዕዘናትን በመገጣጠም ጎነ አራት ፕሌን ቅርፆች ተሰርተዋል።

**ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ**

- ለሕፃናቱ ጎነ ሦስት ቅርፆች የተሰሩትን ፕሌን ቅርፆች (plane figures) ለማሳየት ነው

**ስህተትን መቆጣጠር:**

- ጂኦሜትሪና ተመሳሳይ ነገሮችን ለመስራት -
- ጥቁር መስመርና የተለያዩ ቀለሞች

**ቁምነገሮቹ**

- ቅርፆቹን ማጠዳደር
- የተለያዩ ቅርፆችን እንዴት እንደሚሰሩ መፈተሽ
- አካባቢ አየሩ መመሳሰሉን መመልከት

**ቋንቋ:-**


- የቅርፆችን ስም ማለት:- ካሬ፣ ሮምበስ፣ ፓራሌሎግራም፣ ትራፕዝየምና ሬክታንግል

**ዕድሜ:-**

- 4 ዓመት

## 8. መስራች ጎነ ሦስት ሳጥን ፪

**መርጃ መሳሪያ: -**





- ስምንት ጎነ ሦስት ቅርፆችን የያዘ ሳጥን ሲሆን ሁሉም አንድ አይነት ቀለምና ጥቁር መስመር የላቸውም
- ካሬ ለመስራት የሚጠቅሙ ሁለት ጎነ ሦስት ቅርፆች፤
- ሮምበስ ለመስራት የሚጠቅሙ ሁለት ጎነ ሦስት ቅርፆች፤
- ሬክታንግል መስራት የሚረዱ ሁለት ጎነ ሦስት ቅርፆች፤
- ትራፕዝየም የሚሠሩ ሁለት ጎነ ሦስት ቅርፆች፤

**አቀራረብ:-**

- የመጀመሪያ የማስተዋወቅ እርምጃዎች እንደአለፈው አይነት አቀራረብ ይኖረዋል
- ቁሱን መስየም
- ልክ እንደ ሳጥን አንድ ሁሉ እዚህም ሁሉንም ሦስት ማዕዘን ቅርፆችን ማውጣት
- ትልቁን ቋሚ አንግል፤ ሁለት ጎኖቹ እኩል የሆነ ጎነ ሦስት ቅርፆችን በሕፃኑና በእናንተ ፊት ማስቀመጥ
- ካሬ ሥሩ
- ቀስ ብላችሁ ጎነ ሦስት ምስሉን ለያዩአቸው
- ወዲያው የተሰየ ቅርፅ ስትመለከቱ እዚያው ላይ በመቆም እናንተም ሕፃናቱ እንዲመለከቱ አድርጉ
- እንደገና ካሬ ሥሩ
- ቀጥሎ ጎነ ሦስት ምስሉን ወደ ታች በመገልበጥ ካሬ ሥሩ
- ከዚያ ጎነ ሦስት ምስሉን በተማሪዎች ፊት ባለቀለሙን ወደ ላይ በመገልበጥ ማስቀመጥ
- በተመሳሳይ ሁኔታ በተቀሩት ቅርፆች ላይ መፈፀም
- እንደ ሳጥን አንድ ሂደቱን በቅደም ተከተል መከተል

**መልመጃ 1: -**

- ሕፃኑ ከላይ የተጠቀሰውን አቀራረብ ተከትሎ መስራት አለበት

**ቀጥተኛ ዓላማ**

- የተለያዩ ጎነ ሦስት ምስሎችን በመጠቀም ባለ አራት ጎንና ፖሊጎን ስዕሎችን ይሰራል

**ኢቀጥተኛ ዓላማ**

- ለጂኦሜትሪ ዝግጅት
- ለተመጣጣኝ (equivalence) ምስል ዝግጅት
- ሕፃኑ ጂኦሜትሪ ምስሎች እንዴት በቀጥተኛ መስመር በመጠቀም ጎነ ሦስት ምስሎችን መስራት እንደሚችል

**ቁም ነገር:-**

- በመመራመር የተለያዩ ቅርፆችን እንዴት መገንባት እንደሚቻል ማግኘት

**ቋንቋ:-**

- ሦስት ጎን፣ ካሬ፣ ሮምበስ፣ ሬክታንግል፣ ትራፔዝየም


<u>እድሜ:-</u>

- 4½ አመትና ከዛ በላይ

## 9. <u>መሰራች ጎነ ሦስት ሳጥን 3</u>

*መርጃ መሳሪያ:-*

- ጎነ ሦስት ሳጥን አስር ጎነ ሦስት ምስሎችን የያዘ
- አንድ ትልቅ ግራጫ ሁሉም ጎኖች እኩል የሆነ ጎነ ሦስት
- ሁለት አረንጓዴ እኩል የሆኑ ባለ 90 ድግሪ አንግልና ሦስቱም ጎኖቻቸው የተለያየ ርዝመት ያላቸው ጎነ ሦስት ምስሎች (Scalen Triangle)
- እያንዳንዱ ጎን ጥቁር መስመር ያለው፣ ሁለት እረጃጅም ጎነ ሦስት ቢጫ አንግሎች ከዘጠና ድግሪ በላይ የሆኑ ሁለት ጥቁር መሥመሮች በሁለት ጎናቸው የተሰመረባቸው ጎነ ሦስት ምስሎች



- አራት ቀይ ሶስቱም ጎኖች እኩል የሆኑ ጎነ ሦስት አንዱ ሁሉም ጎኖች ጥቁር መሥመር የተሰመረበት ሲሆን ሦስቱ ግን አንዱ ጎኑ ብቻ ባለ ጥቁር መሥመር ነው

**አቀራረብ**

- ማስተዋወቁ ከበፊቱ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ይቀጥላል
- ቁሶቹን መንገር
- ሁሉንም ጎነ ሦስት ከሳጥኑ ማውጣት
- ምንጣፍ ላይ መደባለቅ
- ለሕፃኑ ግራጫውን ጎነ ሦስት ምስል ማሳየት
- ወደ ጎን በሕፃኑ ፊት ማስቀመጥ
- አረንጓዴውን ጎነ ሦስት ምስል ፊት ለፊታቸው ማስቀመጥ
- ጥቁርን መሥመር መጠቆም
- ከዚያ ቀስ ብሎ ማገናኘት
- አረንጓዴው ጎነ ሦስት በመውሰድ ግራጫው ጎነ ሦስት ላይ ማስቀመጥ
- ከዚያ ህፃኑ እንዴት ወደ ሳጥኑ እንዳሚመለስ ማሳየት፤ ማየት
- በመጀመሪያ ቀይ፤ ቢጫ፣ አረንጓዴውን ግራጫውን በቅደም ተከተል ማሳየት

<u>**ቀጥተኛ አላማ**</u>

- ለጂኦሜትሪ ትምህርት ዝግጁ ይሆናል
- መመጣጠን ያሳያሉ

<u>**ስሕተትን መቆጣጠር**</u>

- ግራጫውን ጎነ ሦስት ጥቁር መስመር ያለው

__ቁምነገሩ__

- ጎነ ሰስቶች የተለያዩ ቅርፆችን መስራት
- ከአካባቢው ጋር መመሳሰላቸውን ማስተዋሉ
- የተላያዩ ቅርፆችን እንዴት መስራት እንዳማችል ዘዴውን ማወቅ


__ቋንቋ__

- የተለያዩ ጎነ ሦስት ስም
- የተለያየ ርዝመት፣ እኩል ርዝመትና አንዱ ማዕዘን ከዘጠና ዲግሪ በላይ የሆነ ጎነ ሦስት ምስል

__ዕድሜ__

- 5 ዓመትና
- ከሳጥን አንድና ሁለት በኋላ

## 10. ባለ ሁለት ኪዩብ



__መርጃ መሳሪያ__

- ባለ ሁለት ኪዩብ የሚቀመጠው በሳጥን ውስጥ ነው
- የተሰራው በአንድ ቀይ ኪዩብ ነው ሶስት ዋነኛ ባለ ሁለት ቀይ ፊቶችና ባለ አራት ጥቁር ጐኖች
- አንድ ሰማያዊ ኪዩብ፣ ሶስት ሬክታንግላዊ ፕሪዝሞች ባለ ሁለት ሰማያዊ ገፆችና አራት ጥቁር ጐኖች
- ➢ ፕሪዝሙና ኪዩቡ የተሰሩት / a+ b/$^2$ ለመገንባት ነው

__አቀራረብ__

- የቁሱን ስም መስጠት
- ሕፃኑ ምንጣፉን እንዲያነጥፍ መንገር
- የት እንደተቀመጠ ለሕፃኑ ማሳየት
- እንዴት ሳጥኑን ወደ ምንጣፉ እንደሚወስድ ማሳየት
- ምንጣፉ ላይ ማስቀመጥ
- ቁሱን በሁለት መስመር መደርደር
- ኪዩቡን ለየብቻ ማስቀመጥ፣ ሰማያዊውን በመጀመሪያ መስመር እንደዚሁም ቀዩን በተመሳሳይ በመጀመሪያ መስመር ማስቀመጥ
- መስመሮቹ የሚከፋፈሉት እንደ ኪዩቡ መጠን በቅደም ተከተል ነው
- ከትልቁ በመጀመር ባለ ሁለት ኪዩብ እንደገና መስራት
- በሳጥኑ ጥግ መልሶ ማስቀመጥ

- የተጋለጠውን ቀዩን ኪዩብ መሸፈን እያንዳንዱ የቀዩ ፕሪዝም ገፅታ የቀይ ኪዩቡን ቀይ ገፅታ መንካት አለበት
- ሰማያዊውና ጥቁሩ ፕሪዝሞች የጥቁር ገጽታ ያላቸው ጥቁሩን ገጽታ በመንካት ማስቀመጥ
- ረጋ ብሎ ቀዩን ኪዩብ በተሰራለት ጥቁር ጥግ ማስቀመጥ
- ከጨረሳችሁ በኋላ ሕፃናቱ ይህንን ተግባር እንዲሠሩ መርዳት
- ሕፃናቱ ቁሳቁሱን እንዴት መደርደሪያ ላይ እንደሚመልሱ ማሳየት

**መልመጃ አንድ -**

- በተመለከተው መሠረት ሕፃኑ ኪዩብ እንዴት እንደሚያንፅ ማየት

**መልመጃ 2 -**

- ኪዩቡ የሚሠራው፣ እንደተመለከተው፣ ከሳጥኑ ውጭ ነው።
- ለሕፃኑ ሁሉም የኪዩቦች ጐን እኩል መሆናቸው ማሳየት
- ኪዩቡን ወደ ላይ በማንሳት ወደ ጐን ተመሳሳይነቱን ማሳየት
- ኪዩቡን በቁመቱ መክፈል
- በተፈለገ መንገድ ኪዩቡ ቢከፈልም አካሄዱ ተመሳሳይ ነው።

**መልመጃ 3**

- ለሕፃናቱ የኪዩቡ ሁለቱ ሽፋኖች እንዴት እንደሚያንፁ ማሳየት
- አንዱ ሽፋን ከቀዩ ኪዩብ በስተቀኝ ሲሆን ሌላኛው ከሰማያዊ ኪዩብ በላይ ነው
- እያንዳንዱን ሽፋን ለየብቻ መገንባትና ሙሉ ኪዩብ ለመስራት ቀዩን ሽፋን መጫን

**ቀጥተኛ አላማ:-**

- የኪዩቡን $(a+b)^2$ እንዲያንፁ ለማብቃት
- ሕፃናቱ ስሜታዊ ልምምድን በባለሁለት ኪዩብ ይለማመዳሉ

**ኢ-ቀጥተኛ አላማ:-**

- ለአልጀብራ መዘጋጀት

**ቁም ነገር:-**

- ባለ ሁለት ኪዩብ መገንባት
- ቅርፆችንና ከለሮችን መለየት

**ስህተትን መቆጣጠር**

- ለይቶ የማየት፣ የሕፃናቱን ችሎታ እና የኪዩቡን ቅርፅ

**ቋንቋ:-**

- ባለ ሁለት ኪዩብ፣ ቀይ ሰማያዊና ጥቁር


**እድሜ:-**

- 4½ - 5 አመት

## 11. ባለሶስት ኪዩብ

<u>መርጃ መሳሪያ</u>:

- ባለ ሶስት ኪዩብ የሚቀመጠው በሳጥን ውስጥ ነው
- ሳጥኑ የያዘው አንድ ቀይ ኪዩብ፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ቀይ ፊትና ጥቁር ጎን ያላቸው ስድስት ሬክታንግላዊ ፕሪዝሞች
- አንድ ሰማያዊ ኪዩብ፣ ስድስት ሬክታንገለዊ ኘሪዝሞች ሲሆኑ መጠናቸው የተለያየ ሰማያዊ ፊትና አራት ጥቁር ጐኖች አሏቸው /ሶስቱ ከሌሎቹ መብለጥ አለባቸው/



- ስድስት ጥቁር ሬክታንግላዊ ፕሪዝሞች
- ጠቅላላ 27 ፕሪዝም $(a + b)^3$

**አቀራረብ**

- አቀራረቡ ከሁለትዮሽ ኪዩብ ጋር ተመሳሳይ ነው
- ነጠላውን ኪዩብ መገንጠልና አራተኛዉ መስመር ላይ ማስቀመጥ
- በመጀመሪያ መስመር ጥቁር ሬክታንግላዊ ከዚያም ሶስት አጫጭር ቀይና ጥቁር ሬክታንግላዊ ፕሪዝም
- በሁለተኛው መስመር ቀይ ኪዩብ ከዚያም ሁሉንም ቀይ ሬክታንግላዊ ፕሪዝም
- በሶስተኛው መሰመር ሰማያዊ ኪዩብ ሶስቱ እረጃጅም ሰማያዊና አንድ ጥቁር ሬክተንግላዊ ፕሪዝምና ሶስት አጭር ሰማያዊና ጥቁር ሬክታንግላዊ ፕሪዝም
- አራተኛው መስመር ቢጫ ኪዩብ ሲሆን ሶስቱ እረጃጅም ቢጫና ጥቁር ሬክታንግላዊ ፕሪዝምና ሶስት አጫጭርና ቢጫ ጥቁር ሬክታንግላዊ ፕሪዝም
- ቀዩን ኪዩብ ሳጥኑ ማእዘን ጥግ በማድረግ ባለ ሶስትዮሽ ኪዩብ መገንባት መጀመር
- ጥቁርና ቀይ ፊት ያላቸውን ፕሪዝም ከቀዩ ኪዩብ ጋር ማዛመድ
- ኪዩብ ለመገንባት ባለ ቀለሞቹን ማዛመዱን መቀጠል
- ኪዩብ ተገንብቶ ሲያልቅ ሕፃኑ ራሱ (ራሷ) እንድትገነባ መጋበዝ ለሕፃኑ ቀዩን ከቀዩ፣ ጥቁሩን ከጥቁሩ፣ ሰማያዊውን ከሰማያዊውና ቢጫውን ከቢጫ አንድ ላይ እንዲያደርጎ ማሳየት
- ካለቀ በኋላ እንዴት መደርደሪያ ላይ እንደሚመልሱ ማሳየት

<u>**መልመጃ 1**</u>:-

- ሕፃናቱ ከላይ እንዳዩት ኪዩቡን እንዲገነቡ

<u>**መልመጃ 2**</u>:-

- ባለ ሦስት ኪዩቦችን ከሳጥኑ ውጪ እንዲገነቡ
- ኪዩቡን ወደ ጎንና ከላይ ወደ ታች መክፈል ይህም ሂደቱ ( **ቅደም ተከተልነቱ** ) ተመሳሳይ መሆናቸውን ለማሳየት ይሆናል

**ስሕተትን መቆጣጠር:-**

- የማየት ችሎታን ማዳበር

**ቋንቋ**

- ባለ ሦስትዮሽ ኪዩብ፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ሰማያዊና ቢጫ

**ዕድሜ:-**

- 4½ - 5 አመት

## 12. ሞቅ ባለ ዉሃ ጣትን ማነቃቃት



**መርጃ መሳሪያ: -**

- ትንሽ ማቅረቢያ (ትሪ) ሙቅ ውሃን በሳህን ውስጥ የያዘ

**አቀራረብ: -**

- ውሃው ሞቅ ያለ መሆኑን ማረጋገጥ
- ፀሐይ ላይ ሊቀመጥ ይችላል

**ቀጥተኛ ዓላማ:-**

- በመንካት አንድን ነገር መልመድን እንዲችሉ ማዘጋጀት

**አቀራረብ:-**

- ከስሜት እንቅስቃሴ በፊት የሚሰጥ
- የት እንዳለ ለሕፃኑ መንገር
- የመንካት ተግባራት ከመፈፀማቸው በፊት ሕፃናት የጣቶቻቸውን ስሜት እንዲረዱና ከዚያ የሚሰማቸው ስሜት በጣም ጥሩና ጣቶቻቸው መልካምና ንፁሕ መሆናቸውን ያረጋግጡ::
- ማቅረቢያውን ጠረጴዛ ላይ ባለው ምንጣፍ ላይ ማስቀመጥ
- የቀኝ እጅ ሁሉንም ጣት ሙቅ ውሃን ውስጥ መክተት
- ቁሱን በመደርደሪያው ላይ በታው ማስቀመጥ
- ሁሉንም የውሃውን ጠብታ ማዕዳት
- ሕፃናቱ እንቅስቃሴውን እንዲቀጥሉ መጋበዝ
- ሕፃናቱ ከጨረሱ በኋላ ሳህኑን በመውሰድ ቆሻሻውን ውሃንበመድፋት መያዣውን ሳህን ማጠብ
- ቁሱን መደርደሪያው ላይ መመለስ

## 13. የሚደሰሱ ሰሌዳዎች



**መርጃ መሳሪያ :-**

- አይን መሸፈኛ፣ ስሜት የሚሰጡ ቁሶች

**ስሌዳ 1:-**

- ሬክታንግላዊ ስሌዳ አንዱ ሻካራ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ለስላሳ

**ስሌዳ 2:-**

- ተመሳሳይ መጠን ያላቸው /ከ9 ክፍሎች 5ቱ ሻካራ የቀረው ለስላሳ/

**ስሌዳ 3:-**

- ከሰሌዳ 2 ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ልዩነቱን ለማየት ከሻካራ ወደ በጣም ሻካራ

**ዝግጅት:-**

- እጆች የፀዱ መሆን አለባቸው /በሙቅ ውሃ/
- ስሜት የሚሰጡ ቁሶች ዝግጁ ይሆናሉ

**አቀራረብ:-**

- ቁሱ የት እንደተቀመጠ ማሳየት
- እያንዳንዱን ሰሌዳ 1 እና 2 ብሎ መሰየም
- ወደ ጠረጴዛ ወይም ወደ ምንጣፍ መውሰድ
- ሕፃኑ አንዱን ሲይዝ የተቀረውን አንተ /አንቺ/ መያዝ አለብህ(ሽ)
- በጣትህ (ሽ) መጀመሪያ መሞከርና ከዚያ ሕፃኑ ተመሳሳይ ተግባር እንዲፈፅም መርዳት

**ስሌዳ 1:-**

- የሰሌዳውን ሻካራ ክፍል ፊት ለፊትህ(ሽ) ሲቀመጥ ሕፃናቱ እንዲመለከቱ መጋበዝ
- አይንን በመሸፈን ወይም በመጨፈን ቀስ በማለት መዳሰስ
- ከለስላሳው ክፍል ወደ ሻካራው ክፍል መሻገር ሰሌዳውንም ሕፃናቱ ፊት በማስቀመጥ እናንተ እንደሞከራችሁ እነርሱም እንዲሞክሩ ማድረግ

**ሰሌዳ 2**

- ከሰሌዳ 1 ጋር በተመሳሳይ ማከናወን
- ከሰሌዳ 2 ፊት ለፊታችሁ አስቀምጡ:: ሕፃኑ አይኑን በተገቢ ሁኔታ መጨፈኑን ተመልከቱ:: ከግራ ጫፍ በመጀመር ቀስ እያለ እጁን ወደ ታች በመውሰድ ሕፃኑ የእናንተ ጣት ወደ አለበት እንዲመጡ መርዳት
- ረጋ ብሎ ሁሉንም እንዲዳስስ መርዳት
- ሁለት ጊዜ ከታች ወደ ላይ መዳሰስ፣ ልጁ በዚህ አይነት መልክ እንዲቀጥል መጋበዝ

**መልመጃ 1: -**

- ሕፃኑ በሰሌዳ 1 እና በሰሌዳ 2 ልክ እንደአቀራረቡ መስራት
- ሕፃኑ ሰሌዳ 1 እና ሰሌዳ 2 ከተለማመደ በኋላ ሰሌዳ 3ን ማስተዋወቅ

**መልመጃ 2: -**

- ሻካራና ለስላሳ የሚለውን ቋንቋ ይማራሉ
- አይን መሸፈኛውን ማስተዋወቅ
- ሕፃኑ ራሱ እንዲሰራ መርዳት

**ቀጥተኛ ዓላማ: -**

- የመንካት ስሜትን ማዳበር
- የመንካት ስሜትን ልዩነቶች እንዲያውቁ መርዳት

- ጡንቻዎቻቸው በመቆጣጠር በቀስታ መዳሰስ እንዲለምዱ ለመርዳት

**ኢ.-ቀጥተኛ ዓላማ፡-**

- ለዕሕፈት መዘጋጀት

**ቋንቋ፡-**

- መንካት፣ ለሌዳ፣ ለስላሳ፣ ሻካራ ወዘተ

**ቁምነገር፡-**

- የሻካራና ለስላሳ ልዩነቶች መለየት አለመቻል


**ስሕተት መቆጣጠር**

- መልመጃ 2ን ተመልከቱ ለምሳሌ ሻካራ፣ ለስላሳ

**ዕድሜ፡-** 3½ እና ከዚያ በላይ

## 14. የዓይን ሽፋንን መጠቀም

**መርጃ መሳሪያ፡-**




- የሚታጠብ ጨርቅ በሬክታንግላዊ ቅርፅ ሁለት ክሮች የተያያዙበት

**አቀራረብ፡ -**

- ለሕፃኑ ቁሱ የት እንደተቀመጠ ማሳየት
- ቁሱን መንገርና ሕፃኑ ወደ ምንጣፉ እንዲወስደው ማድረግ
- በአይን መሸፈኛ መሸፈን
- ለሕፃኑ ሁሉም ነገር እንደነበረ በመንገር በጨዋታ መልክ ማከናወን
- ሳያይ ማጣመድ
- አይን መሸፈኛውን ማንሳትና ሕፃናቱ በተራቸው እንዲያጠልቁት ማድረግ
- ቁሱን መደርደሪያው ላይ እንዲመልሱ ማድረግ

## 15. ተዳባሽ ጠፍጣፋ እንጨት

**መርጃ መሳሪያ፡ -**



- የእንጨት ሳጥን በውስጡ ሬክታንግላዊ ጠፍጣፋ እንጨት የያዘ
- የመሸከር ደረጃቸው የተለያዩ
- በአሸዋ የተሰራው ወረቀት ከበጣም ሻካራነት ወደ ለስላሳነት በደረጃ የተቀመጠ

**አቀራረብ፡ -**

- ሕፃናቱ ከእናንተ ጋር እንዲሆኑ መጋበዝ
- ምንጣፍ እንዲያነጥፉ መንገር

- የእናንተም ሆነ የሕፃኑ እጆች ንፁህ መሆናቸውን እርግጠኞች ሁኑ
- ሳጥኑን እንዴት እንደሚይዙት አሳዩዋቸው
- ምንጣፉ ላይ አስቀምጡት
- በጣቶቻችሁ ንኩት
- ልጆቹም እንደ እናንተ እንዲያከናውኑ ንገሩዋቸው
- በጣም የተለየውን ከሌሎቹ ለይታችሁ ከሳሌዳው ላይ አንሱት
- ፊታችሁ አስቀምጡ
- ከሁሉ በመጀመሪያ በጣት መንካት
- ሕፃናቱ ተመሳሳይ ድርጊት እንዲፈፅሙ መርዳትና ሲያስቀምጡም ከፊተኛው ስር መሆን አለበት
- በአንድ ጊዜ አንዱን ጥንድ በማንሳት እየዳሰሱ ማስቀመጥ
- በዚሁ ጊዜ አምስቱንም በመነካካት ምንጣፍ ላይ ማስቀመጥ
- የተቀሩትን አምስቱን ከሳጥን ውስጥ በማውጣት ምንጣፍ ላይ እንደተገኘ ማስቀመጥ
- አንድ በጣም ለየት ያለውን በማንሳት ፊታችሁ አስቀምጡ
- እንደሌላው ሁሉ በመነካካት እንዲሰማችሁ አድርጉ
- ከግራ አንዱን መውሰድ
- ለየት ብሎ ከተቀመጠው ጎን በማስቀመጥ በመዳሰስ ማየት
- ለየት ያለውን ከዚህኛው ጋር ማወዳደር
- ተመሳሳይ ከሆነ አንዱን ከግራ በመውሰድና ከምንጣፉ በስተቀኝ ማስቀመጥ
- በተመሳሳይ ሁኔታ ማወዳደሩን በመቀጠል ለየት ካለው ጋር የሚመሳሰለውን እስከሚያገኝ ድረስ መፈለግ ከዚያም ፊታችሁ የተቀመጠውን ሕፃናቱ እንዲሞክሩና እንዲያውቁ ማድረግ
- የማይመስለውን በመውሰድ በቀኝ በኩል ማስቀመጥ
- ሕፃናቱም ተመሳሳይ የሆኑትን ጥንዶች እንዲያውቁ አድርጎ ከዚያም አንድ ላይ ያስቀምጡ
- ሁሉም ጥንድ ጥንድ እስኪሆኑ ድረስ መቀጠል
- ከዚያም እንደገና በመዳሰስ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ
- ሕፃናቱ እንደገና እንዲሞክሩ አድርጉ

**መልመጃ 1:-**

- ሕፃኑ በራሱ ጥንድ ተዳሳሽ ጠፍጣፋ እንጨትን ጥንድ ጥንድ አድርጎ ማቅረብ

**መልመጃ 2:-**

- ከመልመጃ አንድ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን እረዳት መምህሩ አይን መሸፈኛውን ማስተዋወቅ አለበት
- ሕፃኑ አይን መሸፈኛውን በመጠቀም መልመጃውን እንዲሰራ ማበረታታት
- ለመጀመሪያ ጊዜ አይን መሸፈኛውን በሚጠቀሙበት ወቅት ከሕፃናቱ ጋር በመቀመጥ ድፍረት እንዲኖራቸው መርዳት

**መልመጃ 3: -**

- ለሕፃኑ እንዴት አድርጎ አምስቱን ተዳሳሽ ቦርድ መለየት እንደሚችል
- አምስቱን ተዳሳሽ ቦርድ በአንድ መስመር በምንጣፉ ጠርዝ በማስቀመጥ መዳሰስ
- አይንን በመጨፈን ከሁሉም ሸካራውን እስኪለዩ ድረስ መዳሰስ
- ከመስመሩ ማውጣት

- ሕፃኑ እንዲዳስስ መጋበዝና ከምንጣፉ ግራ ጠርዝ እንዲያስቀምጥ መርዳት
- የቀሩትን አራቱን በመዳሰስ ቀጥሎ ያለውን ሻካራ መለየት
- ምረጡና ከመጀመሪያው ስር ማስቀመጥ
- ሁለቱንም መንካት
- ሕፃኑ እንዲሞክረው ማድረግ
- ይህንን አይነት ሙከራ በመቀጠል ከበጣም ሸከራ ወደ ሸካራ በቅድም ተከተል ማስቀመጥና ሕፃናቱም እናንተ የሞከራችሁትን ሁሉ እንዲዳስሱ መጋበዝ
- ሁለተኛውን ስብስብ በመውሰድ በረድፍ ማስቀመጥ
- ሕፃኑ በቅድም ተከተል እንዲያስቀምጥ አድርጉ
- ሕፃኑ ከጨረሰ በኋላ ሁሉቱን ስብስብ እንዲሞክር በማድረግ ጥንዶቹ አንድ አይነት መሆናቸውን እንዲረዳ መርዳት
- ከዚያ ሕፃኑ ሁለተኛውን ስብስብ በቅደም ተከተል (ከበጣም ሸካራ ወደ ሸካራ) እንዲያስቀምጥ መጋበዝ

<u>መልመጃ 4፡-</u>

- ሕፃኑ የአይን መሸፈኛውን በመጠቀም ልክ በሦስተኛው መልመጃ የሰራውን እንዲሰራ መርዳት

<u>ቀጥተኛ ዓላማ፡-</u>

- ይህንን የመንካት ስሜትን ማዳበር
- የእጅ ጡንቻዎችን በቀስታ በመንካት መቆጣጠር

<u>ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ፡ -</u>

- ቀስ ብሎ በመንካት ሕፃናትን ለፅህፈት ማዘጋጀት

<u>ስሕተትን መቆጣጠር፡-</u>

- ሕፃኑ የመንካት ስሜቱን ያዳብራል
- በአሸዋ የተሰራውን ወረቀት በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
- የሕፃኑ የማዛመድ ችሎታ

<u>ቁም ነገር</u>

- እንቅስቃሴ ራሱ

**ቋንቋ፡-**

- ሻካራ፣ በጣም ሻካራ፣ አነስተኛ ሻካራ፣ በጣም አነስተኛ ሻካራ

**ዕድሜ፡** - 4½ እና ከዛ በላይ

<u>ጨዋታ አንድ፡-</u>


- ሁለቱን ምንጣፎች አራርቆ ማስቀመጥ
- እነዚህ አንድ ስብስብ አምስት ተዳሳሽ ሰሌዳዎችን በምንጣፉ ላይ ከክፍሉ መጨረሻ ማስቀመጥ
- ሁለተኛውን ስብስብ በተመሳሳይ ማስቀመጥ
- ለሕፃኑ አንዱን እንዲዳስሰው መስጠት
- ሕፃኑ ተመሳሳዩን ከምንጣፉ ፈልጎ እንዲያመጣ መጠየቅ
- የመጀመሪያውን ምንጣፍ ላይ መተውና ሕፃኑ ተመሳሳዩን እንዲፈልግና እንዲያወዳድር መርዳት

- አንድ ላይ ማስቀመጥና ደጋግሞ መሞከር
- ልጆቹ ደስተኛ እስከሆኑ ድረስ መደጋገም

<u>**ጨዋታ ሁለት**</u>:-

- ቁሱ ልክ እንደ ጨዋታ አንድ በስብስቢ ምቀመጥ አለበት
- አንዱ ከመሃከል በማንሳት ሕፃኑ ከዚያ አነስ ያለ ሻካራነት ያለውን እንዲያመጡ መርዳት
- ዘወትር ሕፃኑ ያመጣውን ከሌላኛው ጋር እንዲያወዳድር መፍቀድ

## 16. <u>ጨርቃ ጨርቅ ሳጥን (Fabric Box)</u>



<u>**መርጃ መሳሪያ**</u>:-

- አንድ ትንሽ ጠፍጣፋ ካሬ ሳጥን፤ የሚይዘውም የተለዩ ጥንድ ካሬ ቁርጥራጭ ጨርቃጨርቆች

<u>**ሳጥን 1**</u>

- ከባድ ቁስ በቅደም ተከተል የተዘጋጀ ለምሳሌ ቦብሊን፣ ጥጥ ፍላኔል፣ ፖሊስተር

<u>**ሳጥን 2**</u>

- ከሳጥን አንድ የተጣራ
- የተዘጋጀውን መለየት ያስቸግራል ለምሳሌ ሊነን ናይለን፣ ፍላኔል ጥጥ

**አቀራረብ**

- ሕፃኑን መጋበዝ
- የውጤቱ ሳጥን የተቀመጠበትን ቦታ ሳናይ ስሙን መንገር
- ሕፃኑ ሳጥን አንድን እንዴት እንደሚይዘው ማሳየት
- ምንጣፍ ላይ ማስቀመጥ
- ጣቶቻችሁ እንዲሰማቸው ማድረግ
- እነዚህ የተለያዩ ጥንድ ውጤቶችን በመውሰድ በሁለት እጆቻችሁ መያዝ
- በረድፍ ከምንጣፍ ግራ ጥግ ጫፍ በመጀመር በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
- እያንዳንዱን ጨርቅ በመውሰድ ሳታዩ ዳስሱት
- የተቀሩትንም ከሳጥን ውስጥ በማውጣት ተመሳሳይ ድርጊት ፈፅሙ
- ከጨረሳችሁ በኋላ ከእያንዳንዱ አንድ አንድ ጥንድ በማውጣት ለሕፃኑ የተቀሩት በሙሉ አንድ አይነት መሆናቸውን ማስረዳት
- ሌላ በማውጣት በሁለተኛው ረድፍ ማስቀመጥ
- ብቁ ቦታ ከመጀመሪያው ጎን ለጎን በማጣመድ መጠቀም
- አንድ ከመጀመሪያው ረድፍ በመምረጥ በመዳሰስ ፊት ለፊታችሁ አስቀምጡ
- ሕፃናቱም ዳስሰው ፊታችሁ እንዲያስቀምጡ ጋብዙአቸው
- ሌላ ከሁለተኛው ረድፍ በመምረጥ ከመጀመሪያው ቀኝ ማስቀመጥ
- ሁለቱንም በመዳሰስ ማወዳደር
- ተመሳሳይ ካልሆነ ሁለተኛውን ማስወገድና ከምንጣፍ አናት ቀኝ ጫፍ ጥግ ማስቀመጥ

- መዳሰሱን በዚሁ አይነት ለእያንዳንዱ ተመሳሳይ እስኪገኝ ድረስ መቀጠል
- ተመሳሳይ ካገኛችሁ በኋላ ሕፃናቱ እንዲዳስሱት መጋበዝ
- ጥንዶቹ ከምንጣፍ ቀኝ አናት ማስቀመጥ
- በቂ ቦታ ከሌላችሁ ጥንዶቹን ሳጥኑ ውስጥ ማስቀመጥ ሁሉም ጥንድ መሆናቸውን እናንተም ሆናችሁ ሕፃናቱ እስኪያውቁ ድረስ መቀጠል
- በቂ ቦታ ካለ ጥንዶቹን አንዱን ከሌላው ስር ማስቀመጥ
- የተዛመዱትን ጥንዶች እንደገና ከሕፃናቱ ጋር መዳሰስ
- ለሕፃናቱ እንዴት እንደምናስቀምጥ ማሳየት
- በትክክል ያልተዛመዱትን በሳጥን ውስጥ ማስቀመጥ
- እናንተ እንደፈፀማችሁ ሁሉ ሕፃናቱም እንዲሞክሩ እርዱአቸው

__መልመጃ 1.__

- ሕፃናቱ ከላይ እንደተመለከተው እንዲፈፅሙ

__መልመጃ 2.__

- አይንን በመሸፈን እንዴት ጥንድ ማድረግ እንደሚቻል ለሕፃናቱ ማሳየት
- ይህን ለመፈፀም ሁለት ሕፃናትን መውሰድ፡፡ ለአንዷ ልጅ ጨርቁን አይኗን እንድትሸፍንበት መስጠት ሌላኛዋ ልጅ ተራዋ እስኪደርስ በጥሞና እንድትከታተል ማድረግና ተራዋ ሲደርስ እንድትሰራ መጋበዝ፡፡
- በዚህ መልክ በክፍል ውስጥ ያሉ ህፃናት ሁሉ እንዲሰሩ ማድረግ

**ሳጥን 2**

- እንደላይኛው መስራት

**ቀጥተኛ አላማ**

- በጣት መዳሰስን ይለምዳል

__ኢ ቀጥተኛ አላማ__ የተለያዩ የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችና አይነቶች መኖራቸውን መረዳት

__የሚያስደስተው፡-__

- ውጤትን መርዳት
- የተለያዩ ጨርቃ ጨርቆችን መረዳት
- ማጣመድ /በጥንድ ማስቀመጥ/
- ውጤት

__ስሕተትን መቆጣጠር__

- በመመልከት እና በመዳሰስ

**ቋንቋ ፡-**

- ሲነን፣ ጥጥ፣ ፍላኔል፣ የተቀለመ ፓሊስተር
- ስለ ውጤቱ ፍንጭ የሚገኝበት

**ምሳሌ**

- ከየት ተገኘ

- እንዴት ተሰራ
- የት ነው ተክሉ የበቀለው
- ከመሬቱ አቀማመጥ ጋር የተያያዘ ወ.ዘ.ተ

**ዕድሜ**

- 4½ አመትና ከዛ በላይ

***መልመጃ 1***


- ጥቂት ልጆች፣ ሁለት ምንጣፎችን አራርቀው እንዲያነጥፉ መጠየቅ
- ሳጥን አንድን እንዲያመጡ መጋበዝ
- እያንዳንዱ አንዳንድ ጥንድ እንዲሰሩ መጋበዝ
- አንዱን ውጤት ማንሳትና ስም መስጠት
- ሕፃኑ በመዳሰስ እንዲሰማው ማድረግ
- ሕፃኑ የያዘውን ተመሳሳይ ጥንድ እንዲፈልግ መርዳት ሲሄድ ግን መጀመሪያ የያዘውን ማስቀመጥ አለበት
- ተጣማጁን ካገኘ በኋላ ሁለቱን ውጤቶች ማወዳደርና ሁለቱንም ምንጣፍ ላይ ማስቀመጥ
- አንዱን ውጤት ከመረጣችሁ በኋላ አንዱን ሕፃን በመጥራት እንዲደስስና ተመሳሳይ እንዲፈልግ መርዳት
- ሁሉም ጥንድ እስኪሆን ድረስ ሂደቱን መቀጠል

***መልመጃ 2:-***

- በአንዱ ምንጣፍ ላይ አንዱን ውጤት መስጠትና ተመሳሳይ ውጤት እንዲፈልግ መጠየቅ
- ሕፃኑ ያገኘ ሲመስለው ያገኘውን ውጤት ከአካባቢው ውጤት ጋር ማወዳደር

## ፲፯. <u>የድምፅ ሳጥኖች</u>

***መርጃ መሳሪያ***



- ሁለት የእንጨት ሳጥኖች እያንዳንዳቸው የተለያዩ መጠንኛ ጣሳዎችን የያዙ
- አንዱ ሳጥን ቀይ ክዳን ያለው ሲሆን ሁለተኛ ሳጥን ሰማያዊ ክዳን ይኖረዋል። እያንዳንዱ ሲሊንደር ከሳጥኑ ጋር ተመሳሳይ ክዳን ይይዛል።
- ስትነቀንቁአቸው ድምፅ ይሰጣሉ። እያንዳንዱ ጥንድ የተለያዩ ቀለም ያላቸዉን ጣሳዎች ይይዛሉ።

**አቀራረብ :-**

- ምንጣፍ እንዲያነጥፉ ጋብዙአቸው
- የቁሱን ስም ተናገሩ
- ከሕፃናቱ ጋር ሁለቱንም ሳጥኖች ወደ ሕፃናቱ ምንጣፍ ላይ ውሰዱ

- ሳጥኑን ከቀዩ ክዳን ጋር ፊታችሁ አስቀምጡ
- ክዳኑን ክፈቱና ውስጡ ምን እንዳለ ለሕፃናቱ አሳዩዋቸው
- ክዳኑን ከምንጣፉ ቀኝ ጫፍ ላይ አስቀምጡ
- በጠቋሚ ጣታችሁ መክደኛውን በመጫን እንዲሁም በአውራና በመሃል ጣታችሁ ወገቡን በመያዝ ነቅንቁት
- የመጀመሪያውን በመውሰድ በእያንዳንዱ ሕፃን ጆሮ አጠገብ ሁለት ጊዜ ወደ ላይና ወደ ታች በመወዝወዝ አስሙአቸው
- ልጆቹም ተመሳሳይ የሆነ ተግባር በመፈፀም በሌላኛው ሲልንደር (ጣሳ) እንዲጫወቱ መርዳት
- ሁለተኛውን በመውሰድ ተመሳሳይ ተግባር በመፈፀም በሕፃናቱ እንዲሰሙ ማድረግ ከዚያ ከመጀመሪያው ጣሳ በታች አስቀምጡ:: በሁሉም ሲሊንደሮች ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎችን ፈፅሙ::
- ሰማያዊውን መክደኛ ሳጥን በመውሰድ በሕፃናቱና በእናንተ ፊት ለፊት አስቀምጡት::
- ሕፃናቱ ያለ እረዳት በራሳቸው ተመሳሳይ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ንገሩዋቸው
- እያንዳንዱን ጣሳ በማንሳት በቀይ ክዳን ጣሳ ፊት ለፊት እንደተገኘ መደርደር
- በበቂ እርቀት አራርቃችሁ ማስቀመጣችሁን እርግጣኛ ሁኑ ጥንዶቹን ብቻ መሃል አስቀምጡ::
- ሳጥኑን ሌላኛው አጠገብ ምንጣፉ ላይ አስቀምጡት
- የመጀመሪያውን ቀይ ክዳን ጣሳ በመውሰድ ልክ እንደ በፊቱ ሁሉ ወዝውዙት
- ከዚያም ፊታችሁ በቀኝ በኩል አስቀምጡት
- የመጀመሪያውን ሰማያዊ ጣሳ በመውሰድ ቀይ ክዳን ጣሳ አጠገብ ፊታችሁ አስቀምጡት
- ባለ ቀይ ክዳን ጣሳዎችንና ባለሰማያዊ ክዳን ጣሳዎችን በማወዛወዝ አወዳድሩት
- ተመሳሳይ ከልሆነ ባለ ሰማያዊውን ክዳን ጣሳ ወደ ታችኛው የምንጣፍ ጥግ አስቀምጡ
- ከቀዩ ክዳን ጣሳ ጋር ተመሳሳይ እስክታገኙ ድረስ በዚህ አይነት ማወዳደሩን ቀጥሉ
- ሁለቱን ተመሳሳይ ጣሳዎችን ከምንጣፍ መሃል ከፍ አድርጋችሁ አስቀምጡ
- ቀጥሎ ያለውን ቀይ ክዳን ጣሳ በመውሰድ በተመሳሳይ ሁኔታ አስቀምጡ
- ተመሳሳይ ካገኛችሁ ለሕፃናቱ በመስጠት መመሳሰላቸውን በመስማት እንደያውቁ እርዱአቸው::
- እነዚህን በምንጣፉ መሐል አስቀምጡ
- የተለዩትን ወደ ኋላ አስቀመምጡ
- 12ቱም ጣሳዎች ጥንድ ጥንድ ከሆኑ፣ እያንዳንዱን ጥንድ ነቅንቃችሁ በማድመጥ ተመሳሳይነታቸውን አረጋግጡ
- ሕፃናቱም እንደ እናንተ እንዲፈፅሙ እርዱአቸው
- ጣሳዎቹን ወደ ሳጥን መልሱአቸው ሕፃናቱም በራሳቸው እንዲሰሩ ጋብዙአቸው

*መልመጃ አንድ*

- በአንድ ሳጥን ጣሳዎች መስራት ይቻላል
- አንዱን ስብስብ ጣሳዎች ብቻ በመጠቀም እንዴት እንደሚከፋፈሉ አሳዩዋቸው
- ለሕፃናቱም አሁን እንዴት አድርገን ድምፅ እንደምናገኝ ላሳያችሁ ነው በሉአቸው
- ከፍተኛ ድምፅ በሚሰጥበት ቦታ ላይ ደጋግማችሁ ወዝውዙት
- ለሕፃናቱም አሁን ከፍተኛ ድምፅ ፊታችሁ ከሚገኙት መሀል ለመምረጥ ነው ብላችሁ ንገሩዋቸው

- ተቀራራቢ ድምፅ ያላቸውን ሁለትና ሶስቱን መርጣችሁ ለዩ ከዚያ ከፍተኛ ድምፅ ያለውን በምንጣፉ ላይ አስቀምጡ
- በመንቅንቅ ሁለቱንም አድምጡና ቅደም ተከተሉን አስተወሉ
- በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍተኛ ድምፅ በመምረጥ የተቀሩትን ፊታችሁ አስቀምጡ
- ሕፃናቱም እናንተ እንደሠራችሁት እንዲሰሩ አድርጉ
- ከዚያ በኋላ ሕፃናቱ ሌላኛውን ሳጥን በመጠቀም ይሠራሉ::

**መልመጃ ሶስት** :-

- ሕፃናቱ በደረጃ መከፋፈል ከቻሉ በኋላ በሁለቱ ሳጥን መከተት ይቻላል
- ሕፃናቱ ጥንድ ጥንድ በማድረግ በደረጃ ሁለቱን ስብስቦች በአንድ ላይ እንደ መልመጃ ሁለት ያስቀምጣሉ

**ቀጥተኛ አላማ**:-

የምርመራውን ተግባር ይለማመዷሉ::

- በዚህ አይነት ሕፃናቱ የመስማት ብቃታቸውን ያረጋግጣሉ
- የመያዝ ብቃት ይለማመዳሉ

**ኢ ቀጥተኛ አላማ** :-

- ከቀጥተኛ አላማ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል

**ቁም ነገሩ** :- የሲሊንደሩ ድምፅ በመነቅነቅና በማዛመድ

**ስሕተትን መቆጣጠር** :-

- የሕፃኑን የመስማት ብቃትን ማዳበር
- ሲሊንደርቹም ይቆጠራሉ

**ቋንቋ**

- ከፍተኛ፣ ለስላሳ ድምፆችን: - ከብዙ ልምምድ በኋላ ማወዳደር ማለት: - ከፍተኛ ድምጽ፣ በጣም ከፍተኛ፣ እጅግ በጣም ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣ በጣም ዝቅተኛ፣ እጅግ በጣም ዝቅተኛ የሚለውን በሦስት ክ/ጊዜያት ይማሩታል::

**እድሜ**: - 4 ዓመት እና ከዛ በላይ

**ጨዋታ አንድ**

- ጨዋታው ካለፈው ጋር ተመሳሳይ ነው
- አንዱን የድምጽ ሳጥን ውሰዱና ነቅንቁት
- አንድ የሕፃን ከወዘወዘው በኋላ ተመሳሳዩን ሄዶ እንዲፈልግ አድርጉት

**ጨዋታ ሁለት**: -

- የመሬቱ ምንጣፍ እንዳለፈው ጨዋታ ይዘጋጃል
- አንድ ልጅ አንድ ጣሳ ይመርጣል
- ሁለተኛው ሕፃን ሁለተኛውን ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ድምፅ መርጦ ይዞ እንዲመጣ መንገር

**ጨዋታ ሦስት**


- የሚሰራው ሁለት ምንጣፍ ባላቸው የሕፃናት ሕብረት ነው
- አንዱን ጣሳ ምረጡ
- ሕፃናቱ ከዚህኛው የበለጠ ከፍተኛ ድምፅ ያለውን መርጠው ወደ ምንጣፍ እንዲያመጡ ንገሩዋቸው

- ሌላኛውን ሕፃን ከዚህኛው ዝቅ ያለ ድምፅ መርጦ እንዲያመጣ ጠይቁት
- ልጆቹ ፍላጎት እስከ አላቸው ድረስ ቀጥሉ

## 18. <u>የሽታ ጠርሙሶች</u>

<u>*መርጃ መሳሪያ*</u>

- አንድ ሳጥን፤ ስድስት ሽታ ያላቸውን ጠርሙሶች (ውስጣቸው የሚሸቱ ቅመማ ቅመም የያዙ)



**ለምሳሌ፡ -**

- ደረቅ ዝንጅብል የያዙ ሁለት ጠርሙሶች
- ጥቁር አዝሙድ የያዙ ሁለት ጠርሙሶች
- ነጭ አዝሙድ የያዙ ሁለት ጠርሙሶች
- ሦስት ጠርሙሶች ባለ ቀይ ክዳን
- ሦስቱ ሰማያዊ ክዳን ያላቸው
- ጭንብል (አይን መሸፈኛ)

**አቀራረብ**

- ሕፃናቱን መጋበዝ
- መርጃ መሳሪያው የት እንደተቀመጠ ለሕፃናቱ ማሳየት
- የመርጃ መሳሪያውን ስም መንገር
- ሳጥኑን ምንጣፉ ላይ መውሰድ
- የመጀመሪያው ቡድን ጠርሙሶችን በተርታ ደርድሩ ከዚያ ምንጣፉ ላይ አስቀምጡ
- በመጀመሪያ ቀይ ክዳን ያለውን በማንሳት ፊት ለፊታችሁ አስቀምጡ
- ክፈቱትና ክዳኑን ጠርሙሱ አጠገብ አስቀምጡ
- ጠርሙሱን ቀስ ብላችሁ ነቅንቁትና አሽቱቱ
- የመጀመሪያውን ሰማያዊውን ጠርሙስ ወስዳችሁ በተመሳሳይ ሁኔታ አስቀምጡና አሽቱቱ
- ሕፃናቱም እንዲያሸቱ አድርጉ
- ተመሳሳይ ሽታ ያላቸውን አንድ ላይ አስቀምጡ ተመሳሳይ ካልሆነ ግን ሰማያዊውን ጠርሙስ ከምንጣፉ ታችኛው ጥግ አስቀምጡ
- ሌላኛውን ሰማያዊውን ጠርሙስ በመውሰድ አረጋግጡ
- ተመሳሳይ ከሆነ፣ ጥንድ አድርጋችሁ ከሌሎቹ ጥንዶች በታች አስቀምጡና ሌላኛውን ጥንድ አምጡ ከዚያም የተወገዱትን አምጡ።
- ሁሉም ጠርሙሶች እስኪዛመዱ ድረስ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሉ
- ሕፃናቱም ተመሳሳይ ተግባር እንዲፈፅሙ አድርጉ
- ጠርሙሱን ሳጥኑ ውስጥ ክተቱ
- ሕፃኑ በራሱ እንዲሰራ ንገሩት

***መልመጃ 1***

- ሕፃናቱም እንደ አቀራረቡ እንዲሰሩ አድርጉ

*መልመጃ 2*

- የገላ ሳሙና እንዲለዩ አድርጉ

*መልመጃ 3*

- ልጆቹ የአባባሎቹን አይነት በሽታ መለየት ወደ ሚችሉበት ቦታ መውሰድ
- የመጀመሪያውን አይነት ድርጊት ጭምብል በማድረግ እንዲፈፅሙ መነገር

**ቀጥተኛ አላማ:-**

- ሕፃናቱ በአካባቢው ካሉት ጋር ሽታውንና ድምፅ መስማትን እንዲለማመዱ ማድረግ

**ኢ-ቀጥተኛ አላማ: -**

- የማሽተት ብቃትን ማሳደግ

**ቁምነገር :-**

- ተመሳሳይ ሽታ ያለውን ማዛመድ
- በአካባቢው ውስጥ ያለውን ሽታ መለየት

**ስህተትን መቆጣጠር:-**

- ቁጥጥሩ በጠርሙሶቹ ላይ ነው

**ቋንቋ**

- የቅመሞቹን ስሞች በሦስት ክ/ጊዜ ማስተማር

**ዕድሜ: - 4½ አመትና ከዚያ በላይ**

*መልመጃ 1*

- ምንጣፍ ባላቸው ሕፃናት በህብረት የሚሰራ
- በአንዱ ምንጣፍ አንድ አይነት ሽታ ያላቸው ጠርሙሶች
- በሌላኛው ምንጣፍ ሌላኛው ስብስብ ሽታ ያላቸው
- ሕፃኑ አንዱ ሽታ እንዲያሸት ስጡት
- ከሁለተኛው ምንጣፍ ላይ ሕፃኑ መርጦ የሚመስለውን እንዲያመጣ ጠይቁት
- አንድ ላይ አስቀምጡት
- ሁሉም ጠርሙሶች ስኪዛመዱ ድረስ በዚሁ ዓይነት ቀጥሉ

## 19. የሚሰጥር ቦርሳ (Steriognostic Bags)



*መርጃ መሳሪያ*

- ሦስት ቦርሳዎች
- የመጀመሪያው ቦርሳ የጂኦሜትሪ ቁሶችን ይይዛል
- ሦስት ቡድኖች አሉት
- እያንዳንዱ ቡድን ተመሳሳይ ቁሶች ይኖሩልታል
- ሁለተኛው ቦርሳ የተወሰኑ እቃዎችን ይይዛል ለምሳሌ መቆለፊያ
- በሦስት ነገሮች የተለያዩ ይሆናሉ ለምሳሌ በማገለት፣ በቅርፅና በአይነት

- ሦስተኛው ቦርሳ የተወሰኑ ግዝፈትና ቅርፅ ያላቸውን ይይዛል።

**አቀራረብ፡-**

- በመጀመሪያ መግቢያው ልክ እንደ አለፈው ይሆናል
- ስሙን መንገር
- ሕፃኑ ቦርሳውን ወደ ምንጣፉ እንዲወስድ አድርጉና በጣቱ ይነካካው
- የመጀመሪያው ቦርሳ የያዘውን ቁስ ጠረጴዛ ላይ ዘረግፉት
- ከቡድኑ አንዱን ንኩት ልጆቹም ሌላኛውን ቡድን ይንኩት
- እናንተ አይናችሁን ጨፍናችሁ አንዱን እቃ በማንሳት ነካኩትና ምን እንደያዛችሁ እወቁ
- ምንጣፉ ላይ አስቀምጡት
- ሕፃኑ አንዱን ቁስ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት
- ሁል ጊዜ ሕፃናቱ እንዲሳተፉ አድርጉ
- ተመሳሳይ ቡድን እስኪፈጠር ድረስ በዚሁ አይነት ቀጥሉ
- ልጆቹም በተራቸው እንዲያከናውኑ አድርጉ

**<u>መልመጃ አንድ፡-</u>**

- ሕፃናቱ ከላይ እንደተጠቀሰው እንዲሠሩ ጋብዙዋቸው

**<u>አቀራረብ</u>**

ሕፃናቱ ጭምብል በመጠቀም ከላይ እንደተጠቀሰው ያከናውናሉ

**<u>ቀጥተኛ አላማ፡-</u>**

- የአእምሮ ብቃትንና፣ የማስተዋል ችሎታን ለማዳበር

**<u>ኢ-ቀጥተኛ አላማ፡-</u>**

- ከቀጥተኛ አላማ ጋር ተመሳሳይ ነው

**<u>ቁምነገር</u>**

- የመመራመር ስሜትን ማዳበር


**<u>ቋንቋ፡-</u>**

- የእቃዎቹ ስሞች በሦስት ክ/ጊዜ ይነገራቸዋል

**<u>ዕድሜ</u>** 4 ዓመትና ከዛ በላይ

## 20. እህል መሰየት

**<u>መርጃ መሳሪያ፡</u>**



- ማቅረቢያ አንድ አራት ትናንሽ መያዣዎችን ይይዛል
- ሦስቱ መያዣያዎች፣ ትላልቅ ባቄላዎቹን የያዙ ሲሆን የሚለያዩት በግዝፈት፣ በቀለም፣ በስሪት ይሆናል
- አራተኛው መያዣያ ባዶ ነው

**አቀራረብ፡-**

- የመጀመሪያው ደረጃ ከላይ እንዳየው አቀራረብ ነው

- የእቃውን ስም መንገር
- በጣት መንካት
- ሕፃናቱ ማቅረቢያውን ወደ ጠረጴዛው ይዘው እንዲያመጡ መጠየቅና ጭምብሉንም ማምጣት
- አይናችሁን ጨፍናችሁ አንድ የእህል ፍሬ በመውሰድ በቀኝ እጃችሁ ጠቋሚ ጣት መንካት
- ከዚያም ወደ ነበረበት ቦታ መመለስ
- ተመሳሳይ ተግባር በሁለቱ መያዥያዎች መፈፀም
- ሕፃናቱም ተመሳሳይ ተግባር እንዲፈፅሙ አሳትፋአቸው
- ከእያንዳንዱ መያዥያ በማውጣት በባዶ መያዥያ ውስጥ መጨመር ሆኖም አንዳንድ ፍሬዎች በእያንዳንዱ መያገሮዎች ማስቀረት
- ሕፃናቱ እንዲረዱአችሁ አድርጉ
- አይናችሁን ጨፍናችሁ የመጀመሪያውን የእህል ፍሬ መንካትና ወደ ነበረበት መያዥያ መክተት
- የእህል ፍሬው ተለይቶ እስኪታወቅ ድረስ መቀጠል
- ሕፃናቱ ተመሳሳይ ተግባር እንዲፈፅሙ መጋበዝ

<u>መልመጃ አንድ:-</u>

- ሕፃኑ ከአቀራረቡ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ያከናውናል
- በመጀመሪያ በአንድ ማቅረቢያ
- ቀጥሎ በሁለት ማቅረቢያ

**<u>አቀራረብ</u>**

ሕፃኑ በመልመጃ አንድ መሠረት ጭምብል በመጠቀም መስራት

**<u>ቀጥተኛ አላማ</u>**

- የማዳመጥ ብቃትን ለማዳበር

**ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ**

- ለዕህፈት ማዘጋጀት

**ቁምነገር**

- ስህተትና እንቅቃሴን መቆጣጠር መቻል
- መመልከት


<u>**ቋንቋ:** -</u>

- የጥራጥሬዎቹን ስሞች በሦስት ክ/ጊዜ ማስተማር


<u>**ዕድሜ:**</u> - 4½ ዓመት

## 21. <u>የቅጠል ማስቀመጫ (Leaf Cabinat)</u>

<u>መርጃ መሳሪያ</u>



- ማስቀመጫው ሦስት መሳቢያ ይኖረዋል
- እያንዳንዱ መሳቢያ በስድስት ክፍሎች የተከፋፈለ ነው
- ቀጠን ያለ እንጨት (ልምጭ) በቅርፁ ወይም በፍሬሙ ዙሪያ ማኖር



- የመጀመሪያውና ሁለተኛው መሳቢያ አራት የቅጠል ቅርፆችን ይይዛል
- ሦስተኛው መሳቢያ ስድስት የቅጠል ቅርፆችን ይይዛል

**አቀራረብ ሀ**

- የመጀመሪያው መግቢያ ልክ እንደ ላይኛው አቀራረብ ነው
- ሕፃናቱ አንዱን መሳቢያውን' ወደ ምንጣፉ በማምጣት አንድ ቅርፅ መውሰድ
- በእንጨት ክበቡት
- ከዚያ የቅጠሉን ቅርፅ ቦታው ማስቀመጥ
- አራቱንም የቅጠል ቅርፆች በተመሳሳይ ሁኔታ ማከናወን
- ሕፃናቱም በተመሳሳይ ሁኔታ ሁሉንም መሳቢያ በመጠቀም እንዲያከናዉኑ መርዳት



**አቀራረብ ለ**

- ሁሉንም ቅርፆች ማውጣት
- ምንጣፉ ወይም ጠረጴዛው ላይ በዘፈቀደ ማስቀመጥ
- አንዱን ፍሬም በእንጨት መሙላት
- ተመሳሳዩን ቅርፅ በእንጨት ሙሉትና ወደ ቦታው መልሱት
- የቀሩትንም በተመሳሳይ ሁኔታ አከናውኑት
- ሕፃናቱን አሳትፉ
- በመጨረሻ ሕፃናቱ በእያንዳንዱ መሳቢያ ይሠራሉ፤ ከዚያም በአንድ ጊዜ በሁለት መሳቢያዎች ይሰራሉ።

**ቀጥተኛ ዓላማ:-**

- በውጪ ያለውን ትክክለኛ መልመጃ ለመጠቆም

**ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ:-**

- ለመፃፍ መዘጋጀት

**ስሕተትን መቆጣጠር:-**

- በቁሱ ውስጥ

**ቋንቋ: -**

- ከብዙ ልምምድ በኋላ የቅጠሎቹን ስሞች በሦስት ክ/ጊዜ ይማራሉ።
- ማስወገድ፤ ጭስ፤ አልባ፤ ሶስት ጎናም ወዘተ

**ዕድሜ:-** 4 ዓመትና ከዚያ በላይ

## 22. ቅጠልማ ቅርፅ



**መርጃ መሳሪያ:-**

- በሦስት ሳጥኖች በመክተት የቅጠል ቅርፅ ያላቸውን የካርድ ስብስብ በካቢኔት ውስጥ ማስቀመጥ

**ስብስብ አንድ**

- ሁሉም በአንድ ቦታ ይሰበሰባሉ

**ስብስብ ሁለት:-**

- ድንበሩን በግልፅ መስመር ማሳየት

**ስብስብ ሦስት:-**

- ድንበሩን በቀጭን መስመር ማሳየት

**አቀራረብ ሀ:-**

- ካርዱን ለሕፃናቱ ማስተዋወቅ
- የመጀመሪያውን የካርድ ስብስብ መግለፅ
- ምንጣፉ ላይ እንዲያደርጉ ሕፃናትን መጋበዝ
- ሕፃናቱ አንዱን መሳቢያ እንዲያመጡ አድርጉአቸው
- አንዱን ካርድ በሌላኛው ካርድ ላይ ይደራርቡት
- አንዱን ካርድ ማንሳት
- ሕፃናቱ ቅርፁን እንዲመለከቱ አድርጉ
- ተመሳሳዩን ቅርፅ ሄደው ከካቢኔቱ እንዲያመጡ ሕፃናቱን ጠይቋቸው ከዚያ መመሳሰላቸውን አረጋግጡና ደራርቧቸው
- ካቢኔቶቹ ውስጥ ያለውን ካርድ መተው
- ሕፃናቱም በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲቀጥሉ እርዱአቸው

**አቀራረብ ለ:-**

- ሁለት ምንጣፎችን አንጥፉ
- የመጀመሪያውን የካርድ ስብስብ በሚያመች መንገድ ምንጣፉ ላይ መደርደር
- እንደ ሕፃናቱ ችሎ እና ብቃት የተለያዩ መሳቢያዎችን ማዘጋጀት
- ሕፃናቱ አንዳንድ ቅርፅ ከመሳቢያ በመውሰድ ዙሪያውን በእጅ ይነካኩት
- ሕፃናቱ ወደ ምንጣፉ በመሄድ ተመሳሳይ የሆነውን ካርድ ይምረጡና ያምጡ
- ተመሳሳይ መሆናቸውን ለማወቅ አንዱን አንዱ ላይ በመጫን ማረጋገጥ
- ሕፃናቱ ሁሉንም ቅርፆች በተመሳሳይ ሁኔታ ይሞክሩ

**ቀጥተኛ ዓላማ:-**

- የማየት ብቃት ማዳበሪያ ልምምድ ያገኛሉ

**ኢ-ቀጥተኛ ዓላማ**

- ከቀጥተኛ ዓላማ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል

**ስሕተትን መቆጣጠር**

- መመልከት፣ ማስተዋል

**ቁምነገር: -**

- እንቅስቃሴውና የመምረጥ ብቃቱ

**ዕድሜ:-**

- ሕፃናቱ ከተለያዩ ቅርፆች ጋር በብዛት ከሠሩ በኋላ